# ምዕራፍ ሶስት

## ስነ-መዋቅር

### *መግቢያ*

ባለፈው ምዕራፍ ሰለ እማርኛ ቃላት አከፋፈልና በየክፍሉ ሰለሚገኙት ቃላት የርባታና የምስረታ ሰርዓት ተወያይተናል። ትኩረታችን በቃላቱ ውስጣዊ ስርዓት ላይ ነበር። ሰርዓቱ በየክፍሉ ውሰጥ የሚገኙት ቃላት ከምንና እንዴት እንደሚመሰረቱ የሚያሳይ ነበር። ለምሳሌ፤ እንደ <u>ደግነት</u> ያሉ ቃሰተ <u>ደግ</u> ከሚለው ቅፅላዊ ነፃ ምዕላድና /-ንንኧት/ ከሚሰው ዕስር መሰራች ምዕላድ ላይ የተፈጠሩ የስም ክፍል ቃላት እንደሆኑ ተመልክተናል። የአቀነጃጀታቸው ስርዓትም ከነፃው ቅፅላዊ ምዕላድ ቀኝ ጉን ላይ /-ንንኧት/ የሚሰውን ዕስር ምዕላድ መቀጠል ነው።


በዚህ ሁኔታ የሚፈጠሩ ሰሞች ሰመደብ፣ ሰቁጥር፤ ሰፆታ፤ ሰሙያ፣ ወዘተ፣ ይረባሉ። ይህን ሲያደርጉም ቅርፃቸውን በከፊል እንደሚለዋውጡ አይተናል። ሁኔታውን ይበልጥ ሰመረዳት <u>ደግነት</u> የሚሰውን ስም ርባታ ከዚህ ቀጥሰን እናሳያሰን።

| መደብ | | | 1 |
|---|---|---|---|
| 1ኛ | | ደግነት-ኤ | |
| 2ኛ | ተ | ደግነት-ሀ | |
| | አ | ደግነት-ሀ-ኢ > ሽ | |
| 3ኛ | ተ | ደግነት-ኡ | |
| | አ | ደግነት-ኡ-አ | |
| | ብ | ደግነት-አች-ን | |
| | | ደግነት-አች-ሀ-ኡ | |
| | | ደግነት-እች-ኧ-ኡ | |

የርባታውን ስርዓት ሰናይ እንደ /-ኤ/፥ /-ሀ/፥ ወዘተ፥ ያሉ ቅጣይ የርባታ ምዕሳዶች ቀደም ሲል <u>ደግ</u> ከሚሰው ቅፅል ላይ /-ንንኧት/ በሚሰው መስራች ምዕላድ አማካኝነት ከተመሰረተው፥ <u>ደግነት</u> ከሚሰው ሰም ቀኝ ጉን ላይ እንደሚቀጠሉ

እንረዳለን። ስለዚህ ሁኔታ የሚፈጠሩትና የሚረቡትን ቃላት ውስጣዊ ስርዓት በጥቅሉ እንደሚከተለው እናሳያለን።

2




እንግዲህ ባለፈው ክፍል የተመለከትነው እንደዚህ ያሉ ቃላትን ያወቃቀር ስርዓት ሲሆን፣ በዚህ ክፍል ደግሞ ቃላት ብቻቸውን እየቆሙ፣ ወይም ከሀረግ ጋር እየተቀናጁ ሰፋ ሰፋ ያሉ መዋቅሮችን እንዴት እንደሚመሰርቱ እንመለከታለን። ከላይ በሚታየው ሁኔታ፣ ምዕላድ ከምላድ ጋር ሲቀናጅ ቃል እንደሚፈጥር ሁሉ፣ ቃልም ከሀረግ ጋር ሲቀናጅ ከቃል ከፍ ያለ መዋቅርን ይፈጥራል። ምዕላድ ከምዕላድ ጋር እየተቀናጁ ቃል የሚፈጥሩበት ስርዓት ስነ-ቃላት እንደሚባል ሁሉ፣ ቃላት ከሀረግ ጋር እየተቀናጁ ሰፋፊ መዋቅርን የሚፈጥሩበት ስርዓትም ስነ-መዋቅር ይባላል። ባለፈው ክፍል በስነ-ቃላቱ ላይ እንዳተኮርን ሁሉ፣ በዚህ ክፍል በስነ-መዋቅሩ ላይ እናተኩራለን።

ባለፈው ክፍል እንዳደረግነው፣ በዚህ ክፍልም እያንዳንዱን የቃላት ክፍል በየተራ እየወሰድን በውስጡ የሚገኙ ቃላት ከክፍላቸው ወይም ከሌላ ክፍል ሀረጎች ጋር እንዴት እንደሚቀናጁ፣ ማለትም እንደሚዋቀሩ ለማየት እንሞክራለን።

## *ሀረግ*

ሀረግ የምንለው አንድን ከቃል የሰፋ፣ ከአረፍተ ነገር ያነሰን መዋቅር ነው። ከዚህ ላይ አንድ ነገር ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይኸውም በመዋቅርና በሀረግ መካከል ያለውን ልዩነት የሚመለከት ነው። መዋቅር አጠቃላይ ቃል ነው ፣ ማንኛውንም ቅንጅት ያካትታል። ለምሳሌ፣ በስነ-ድምፅ ደረጃ የቀለምን፣ በስነ-ቃላት ደረጃ የቃላትን፣ እንደዚሁም በስነ-መዋቅር ደረጃ የሀረግንና የአረፍተ ነገርን ውስጣዊ ቅንጅት

ይመለከታል። ሀረግ ግን ውስን ነው። ውስንነቱም በሁለት ወገን ነው። በአንድ ወገን በአይነቱ ወይም በክፍሉ ሲሆን፣ በሌላ ወገን በይዘቱ፣ ማለትም በመጠኑ ነው። በክፍሉ ሲታይ፣ አንድ ሀረግ ስማዊ፣ ግሳዊና ቅፅላዊ፣ ወዘተ፣ ሲሆን ይችላል። ስለዚህም ስማዊ ሀረግ፣ ቅፅላዊ ሀረግ፣ ወዘተ፣ እያልን አንዱን የሀረግ አይነት ከሌላው እንለያለን።

የሀረጉ አይነት የሚወሰነው በቋንቋዋው ውስጥ በሚገኙት የቃላት ክፍሎች መጠን ነው። አንድ ቋንቋ አምስት የቃላት ክፍሎች አሉት ብንል፣ የሀረጉ አይነትም እንደዚሁ አምስት ይሆናል። ባለፈው ክፍል የአማርኛ ቃላት በስድስት እንደሚከፈሉ አይተናል። በለዚህም ቋንቋዋው ስድስት የሀረግ አይነቶች ይኖሩታል። እያንዳንዱ የቃላት ክፍል በውስጡ ከሚገኘው ቃል ላይ ሀረግ የመመስረት ዕድል አለውና። ባለፈው ንዑስ ክፍል፣ ቃላት በቅለው ሀረግ ሊሰዱ ይችላሉ ብለን ነበር። ለምሳሌ፣ አንድ ስም የሆነ ቃል፣ አድጎ ሀረግ ሲሰደ፣ ስማዊ ሀረግ ይሆናል። ይህ እንግዲህ ከአይነት አንፃር ሲታይ ነው።

ከመጠን አኳዋያ ሲታይ ደግሞ፣ አንድ ሀረግ ንዑስ ወይም አቢይ ሲሆን ይችላል። ይህ የሚወሰነው በሀረጉ ውበጣዊ ይዘት ነው። ትንሽ ነገሮችን የያዘ ንዑስ ሲባል፣ በርካታ ነገሮችን የያዘ አቢይ ሀረግ ይባላል። ይህን ወደ ዝርዝሩ በንገባ እናየዋለን። ከዚህ ላይ ለመግለፅ የምንፈልገው ንዑስም ይሁን አቢይ ሀረግ በቃል ላይ የተመሰረተ የመዋቅር አይነት መሆኑን ነው።

## *ስማዊ ሀረግ*

ስማዊ ሀረግ የምንለው ከአንድ ስምና ከሌሎች ሀረጎች የሚፈጠርን መዋቅር ነው። የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

የሳር ቤት 1

ይህ የስማዊ ሀረግ መዋቅር ነው። የተዋቀረውም ቤት ከሚለው ስምና <u>የሳር</u> ከሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። ስሙ ከሀረጉ ጋር ተቀናጅቶ አንድ ከቃል በላይ ያለ አሀድ ፈጥሯል። ይህም አሀድ የሳር ቤት የሚለው መዋቅር ሲሆን፣ በአይነቱ ስማዊ፣ በመጠኑ ደግሞ ሀረጋዊ ነው። ከቃል ይበልጣል ማለት ነው።

ከዚህ ላይ አሁንም ሁለት ነገሮችን ከወዲሁ ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የመጀመሪያው ማንኛውም ሀረግ ከመሪ ቃልና ከሀረግ የሚፈጠር መሆኑ ነው። ቃሉ ለሚፈጠረው ወይም ለሚመዘዘው ሀረግ ዘር ሲሆን፣ ሀረጉ ደግሞ አሳዳጊው ነው። የሚያሳድገውም ልዩ ልዩ መግለጫ ስለዘሩ በመስጠት ነው። ሁለተኛው ጉዳይ ከስሙና ከሀረጉ የሚፈጠረው መዋቅር አንድ አሀድ ለመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው? ከሚል ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነው። ጥያቄው መሰረታዊ ነው። ወደፊት በየደረጃው አንድ አሀዳዊ መዋቅር ነው፣ እያልን የምንለየውንና የምንተነትነውን መዋቅር ሁሉ የሚመለከት ስለሆነ፣ ከወዲሁ ውል ያለው ምላሽ ማግኘት አለበት።

በመሰረቱ፣ አንድ ዘር ቃልና አንድ ሀረግ ሲቀናጁ፣ የሚፈጠረው ቅንጅት አንድ አሀዳዊ መዋቅር ነው የምንለው፥ ቅንጅቱ የሚከተሉትን መሰፈርቶች በከፊል ወይም በሙሉ የሚያሙዋላ ከሆነ ነው።

(ሀ) ቅንጅቱ በአረፍተ ነገር ውስጥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንዳሰ፣ ማለትም ከተዋቃሪዎቹ መካከል አንዱም ሳይቀር፣ ሲንቀሳቀሰ ከቻለ፤
(ሰ) ቅንጅቱ በሙሉ በአንድ *ተውላጥ* (ትክ) ሊተካ ከቻለ፤
(መ) በአረፍተ ነገር ውስጥ፣ ቅንጅቱ ያለምንም ቀሪ ሲገደፍ ከቻለ፥
(ለ) በውስጡ ሌላ ቃል የማያሰገባ ከሆነና
(ረ) ቅንጅቱ እንደ እና ባሉ አያያዥ ቃላት አማካኝነት ከሌላ አቻ ቅንጅት ጋር ሲዋቀር የሚችል ከሆነ።

ከነዚህ መሰፈርቶች አኩዋያ እሰቲ ከላይ በተራ ቁጥር (1) የተሰጠውን ምሳሌ እንደ እሀዳዊ መዋቅር (ቅንጅት) መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንመርምር።

የመጀመሪያው መሰፈርት አንድ ቅንጅት አንድ አሀዳዊ መዋቅር ነው የሚባለው በአንድ ላይ ሊንቀሳቀሰ ከቻለ ነው የሚል ነው። ከዚህ አንፃር የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) [ካሳ የሳር ቤት ነበረው] 2
(ለ) የሳር ቤት [ካሳ — ነበረው]
(መ) * የሳር [ካሳ — ቤት ነበረው]
(ሰ) * ቤት [ካሳ — የሳር ነበረው]

ቅንፉ የሚያመለክተው የአረፍተ ነገሩን መጀመሪያና መጨረሻ ነው። በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፥ የሳር ቤት የሚለው ቅንጅት ካሳ ከሚለው ስም ቀጥሎ ገብቶአል። በምሳሌ (ለ) ውስጥ ግን ይኸው ቅንጅት የገባው ካሳ ከሚለው ስም በፊት፣ ማለትም ከአረፍተ ነገሩ ውጭ ነው። ይህም በመሆኑ፣ በምሳሌ (ሀ) ውስጥ የሳር ቤት የሚለው ቅንጅት የነበረበት ቦታ፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ ክፍት ሆኖ ይታያል። ይህም የሚያመለክተው፣ ቅንጅቱ በምሳሌ (ሀ) ውስጥ ከነበረበት መሰረታዊ ቦታ ተነስቶ ወደ አረፍተ ነገሩ ውጭ መሄዱን ነው። ነጠብጣቦቹም የሚያመለክቱት መሰረታዊ ቦታው መለቀቁን ነው። መዋቅሩ የተንቀሳቀሰው እንደ አንድ እሀድ ነው። በመሆኑም አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት ሊኖረው ችሎአል። ምሳሌ (መ) እና ምሳሌ (ሰ) የተዛቡ አረፍተ ነገሮች ናቸው። የተዛቡበት ምክንያት የሳር ቤት በሚለው ቅንጅት ውስጥ የሚገኙት ክፍሎች በአንድ እሀድነት ሳይሆን፣ በተናጠል በመንቀሳቀሳቸው ነው። ይኸውም በምሳሌ (መ) የሳር የሚለው ብቻውን፣ በምሳሌ (ሰ) ቤት የሚለው እንደዚሁ ብቻውን ተንቀሳቅሶአል። ይህም የተናጠል እንቅስቃሴ ለአረፍተ ነገሮቹ መዛባት

ምክንያት ሆኖአል። በምሳሌ (ለ) ውስጥ እንደሚታየው፣ <u>የሳር ቤት</u> የሚለው እንዳለ ሊንቀሳቀስ መቻሉ፣ እንደ አንድ አሀዳዊ መዋቅር ሊያስቆጥረው ይችላል።

ሁለተኛውን መሰፈርት እንመልከት። ይህም አንድ ቅንጅት እንዳለ በአንድ ተውላጥ ሊተካ ከቻለ፣ እንደ አንድ መዋቅር ሊቆጠር ይችላል የሚል ነው። ከዚህ አንፃር አሁንም የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [የሳር ቤት] አለው 3
(ለ) [እሱም] ቀበሌ 13 ውስጥ ይገኛል
(መ) * [ የሳር እሱም] ቀበሌ 13 ውስጥ ይገኛል

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ ያለው [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ [እሱም] በሚለው ተውላጥ ተተክቶአል። ተውላጡ የተካው ቅንጅቱን በሙሉ ነው። ስለዚህም ምሳሌ (ለ) ተቀባይነት ያለው አረፍተ ነገር ነው። በምሳሌ (መ) ውስጥ ግን፣ ተውላጡ የተካው [የሳር ቤት] የሚለውን ቅንጅት በሙሉ ሳይሆን፣ የቅንጅቱ አንድ አካል የሆነውን [ቤት] የሚለውን ስም ብቻ ነው። በመሆኑም አረፍተ ነገሩ ሊዛባና ተቀባይነትን ሊያጣ ችሎአል። ይህም የሚያሳየው [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት በሙሉ እንጅ፣ በከፊል ብቻ በተውላጥ ሊተካ አለመቻሉን ነው። ይህም ቅንጅቱ አንድ አሀዳዊ መዋቅር እንደሆነ ያመለክታል። ወደ ሶስተኛው መስፈርት እንሂድ።

መስፈርቱ አንድ ቅንጅት እንዳለ ሊገደፍ ከቻለ፣ እንደ አንድ መዋቅር ሊቆጠር እንደሚችል ይገልፃል። ከዚህም አንፃር የሚከተሉትን ምሳሌዎች ደግሞ እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [የሳር ቤት] ነበረው 4
(ለ) አስቴርም [—] ነበራት

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ የሚታየው [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት በምሳሌ (ለ) ውስጥ በቦታው የለም፣ ተገድፎአል ማለት ነው። የተገደፈውም በሙሉ እንጅ በከፊል አይደለም። በሙሉ ሊገደፍ መቻሉ፣ ቅንጅቱ አንድ አሀዳዊ መዋቅር እንደሆነ ያመለክታል።

አራተኛውን መስፈርት ደግሞ እንመልከት። ይህም አንድ ቅንጅት አንድ አሀዳዊ መዋቅር ከሆነ፣ በመካከሉ ሌላ ቃል ጣልቃ ሊያስገባ እንደማይችል ይገልፃል። ስለዚህ የሚከተሉትን በአሰረጅነት እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [የሳር ቤት] አለው 5
(ለ) ? ካሳ [የሳር <u>ትንሽ</u> ቤት] አለው

ምሳሌ (ሀ) ተቀባይነቱ የማያጠራጥር አረፍተ ነገር ነው። ምሳሌ (ለ) ግን ተቀባይነቱ አጠያያቂ ነው። በሁለቱ ምሳሌዎች መካከል ያለው ልዩነት፣ በ(ለ) ውስጥ፣ <u>ትንሽ</u>

የሚለው ቃል [የሳር ቤት] በሚለው ቅንጅት ውስጥ ጣልቃ መግባቱ ነው። የዚህ ቃል ጣልቃ መግባት አረፍተ ነገሩን ሊያዛባውና ተቀባይነቱን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባው ችሎአል። ቃሉ በቅንጅቱ መካከል ሳይሆን፣ በመነሻው ላይ ቢገባ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት ይኖረዋል። ይህም እንደሚከተለው ሲሆን ነው።

ካሳ [ትንሽ [የሳር ቤት]] አለው 6

የምሳሌ 5(ለ) ተቀባይነት አጠያያቂ መሆን፣ በአንፃሩ ደግሞ የምሳሌ (6) ትክክል መሆን የሚያመለክተው፣ [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት፣ በውስጡ ሌላ ቃል ሊያስገባ አለመቻሉን ነው። ይህም ቅንጅቱ እንድ አሀዳዊ መዋቅር እንደሆነ ያመለክታል።

የመጨረሻው መስፈርት እንድ ቅንጅት አሀዳዊ መዋቅር ከሆነ፣ እንደ እና ወይም ባሉ አያያዥ ምዕላዶች ሊቀናጅ የሚችለው ከእቻ መዋቅር ጋር ብቻ እንደሆነ ይገልፃል። በዚህ መስረት የሳር ቤት የሚለው ቅንጅት ሊያያዝ የሚችለው እንደ የቆርቆሮ ቤት ካለ አቻ ቅንጅት ጋር ነው። ይህም እንደሚከተለው ነው።

(ሀ) [የሳር ቤት] እና [የቆርቆሮ ዳስ] 7
(ለ) ?[የሳር ቤት] እና [ዳስ]

የምሳሌ 7(ለ) ተቀባይነት አጠራጣሪ ነው። ምክንያቱም የሳር ቤት የሚለው ቅንጅት የተያያዘው ዳስ ከሚል ተራ ስም ጋር በመሆኑ ነው። ዳስ የሚለው ተራ ስም ሊያያዝ የሚችለው እንደሱ ተራ ከሆነ ስም ጋር እንጅ፣ እንደ የሳር ቤት ካለ ስሬ ቅንጅት ጋር አይደለም። እንደ ቤት ካለ ተራ ስም ጋር ሲያያዝ፣ የሚከተለውን ይመስላል።

ቤት እና ዳስ 8

ይህ ተቀባይነት ያለው መዋቅር ነው። ሁኔታው "ያላቻ ጋብቻ... " ጥሩ አይሆንም የሚለውን ተረትና ምሳሌ ሊያስታውሰን ይችላል፡፡

እንግዲህ [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት ከፍ ሲል ከ(ሀ) እስከ (ረ) ድረስ የተዘረዘሩትን የመዋቅር መስፈርቶች ስለሚያሟላ እንደ አንድ አሀዳዊ መዋቅር ሊቆጠር ይችላል። ማንኛውም እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ ቅንጅት ሁሉ፣ እንደዚሁ እንደ አንድ መዋቅር ሊቆጠር ይችላል። ወደፊት መዋቅር እያልን የምን ጠቅሳቸው ቅንጅቶች ሁሉ፣ ከነዚሁ መስፈርቶች አኳያ የሚታዩ መሆናቸውን ከወዲሁ እንገልፃለን። አሁን ከፍ ሲል ወደጀመርነው የመዋቅር ጉዳይ እንመለስ።

ከላይ ለመጠቆም እንደሞከርነው፣ በማንኛውም መዋቅር ውስጥ የሚገኝ ክፍል ተዋቃሪ ይባላል። ማንኛውም መዋቅርም የተዋቃሪዎች ቅንጅት ነው። አንድ ተዋቃሪ በመዋቅር ውስጥ የሚገኝበት የተለየ ቦታና ተግባር አለው። ተግባሩ የመዋቅሩ መሪ ወይም ተመሪ መሆን ነው። ለምሳሌ በ5(ሀ) ውስጥ [የሳር ቤት] የሚለው መዋቅር ተዋቃሪዎች ቤት የሚለው ስምና የሳር የሚለው ህረግ ናቸው። አቀማመጣቸው የሳር የሚለው ቀድሞ፣ ቤት የሚለው እሱን ተከትሎ በመምጣት ነው። በዚህ አቀማመጥ፣

<u>ቤት</u> የሚለው ተዋቃሪ ተግባር አጠቃላይ መዋቅሩን መምራት ነው። የመዋቅሩ ምሰሶ ነው፣ ለማለት ይቻላል። ያለሱ መዋቅሩ ብቻውን አይቆምም። ስለዚህም የመዋቅሩ <u>አይቀሬ</u> አካል ወይም ተዋቃሪ ነው። <u>የሳር</u> የሚለው ተዋቃሪ ተግባር መሪውን፣ ማለትም <u>ቤት</u> የሚለውን ስም ማጀብ ነው። አጅቦም [የሳር ቤት] የሚለውን ስማዊ ሀረግ ይመሰርታል። ያለመሪው ብቻውን ይህን ሊያደርግ አይችልም። መሪው ስም ግን ያሳጃቢው ብቻውን እንደ ምሰሶ ሊቆምና ሀረግ ሊሆን ይችላል። ስፌ መዋቅር ግን ሊሆን አይችልም፣ አጃቢ የለውምና። በዚሁ መሰረት ወደፊት እንደ ምሰሶ ብቻቸውን እየቆሙ የምናገኛቸውን አሀዶች ሀረግ እያልን እንጠራቸዋለን። ስራዊቱ እንደከዳው የጦር መሪ ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡

መሪው ከአጃቢ ጋር ሲዋቀር፣ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ አጃቢውን በስተግራ አስከትሎ እሱ በስተቀኝ ቀድሞ በመገኘት ነው። መሪው ከአጃቢው ቀድሞ በስተቀኝ ስለሚገኝ ሀረጉ ቀኝ መሪ ሀረግ ይባላል። ይህም ባለፈው ክፍል ስለ ጥምር ቃላት ስንወያይ እንዳየነው የተጣማሪዎች አሰላለፍ መሆኑ ነው። በአጃቢው መነሻ ላይ የምትገኘው "የ" ባለፈው ክፍል ያየነውን ዘርፍ ሙያን አመልካች ምዕላድ ነች። እሰዋ የምትገኝበት ስም ሙያው ባለቤት ወይም ተሳቢ ሳይሆን ዘርፍ ነው[1]። ይህን ወደፊት በስፋት እናየዋለን። ለጊዜው ግን ተግባርዋ አጃቢው ስም፥ ማለትም <u>ሳር</u>፥ የመሪው አካል ሆኖ ሀረጉን መመስረቱን ማመልከት ነው፣ ብለን፣ ከፍ ሲል ወደ አነሳነው የመሪና የተመሪ (አጃቢ) ተግባር እንመለስ።

አንድ መሪ የሀረግን አይነት ብቻ ሳይሆን፣ ክፍሉንም ይወስናል። መሪው ስም ከሆነ፥ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ ይሆናል። መሪው ግስ ከሆነ፣ መዋቅሩም እንደዚሁ ግሳዊ ሀረግ ይሆናል። ከዚህ አንፃር ከላይ የተጠቀሰው ምሳሌ መሪ <u>ቤት</u> የሚለው ስም ስለሆነ፣ ሀረጉ ስማዊ ነው።

የሚከተለውን ደግሞ እንመልከት።

ትልቅ ቤት 9

ይህ መዋቅር <u>ትልቅ</u> የሚለው ቅፅልና <u>ቤት</u> የሚለው ስም ቅንጅት ነው። የመዋቅሩ መሪ አሁንም <u>ቤት</u> የሚለው ስም ሲሆን፣ አጃቢው <u>ትልቅ</u> የሚለው <u>ቅፅል</u> ነው። መሪው ስም ስለሆነ፣ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ ነው። ከዚህ ሁኔታ የምንረዳው፣ የአንድ መዋቅር መሪ ስም እስከሆነ ድረስ፣ አጃቢው ምንም ይሁን ምን፣ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ እንጅ ሌላ ሊሆን አይስመቻሉን ነው ።

በምሳሌ (1) እና (7) ውስጥ መሪው የተዋቀረው ከአንድ አጃቢ ጋር ብቻ ነው። ይህ ሁኔታ ግን አንድ መሪ ከአንድ በላይ አጃቢ አይኖረውም ወደሚል

---

[1] የ "የ"ን የተለያየ ተግባር በተመለከተ አሁንም ሀይሉ (1967)ን ይመልከቱ።

ድምዳሜ አይወስድም፣ ብዙ አጃቢ ሊኖረው ይችላል፤ እንደ ትልቅ መሬ። ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት።

ትልቅ የሳር ቤት 10

ይህ አንድ መዋቅር ነው። መሪው አሁንም ቤት የሚለው ስም ስለሆነ፣ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ ነው። መሪው ሁለት አጃቢዎች አሉት። እነሱም የሳር የሚለው ስማዊ ሀረግና ትልቅ የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ ናቸው። በምሳሌ (1) ውስጥ የሳር ቤት የሚለው ቅንጅት ራሱን የቻለ ስማዊ ሀረግ እንደሆነ ከፍ ሲል አይተናል። በዚህ ምሳሌ ውስጥ ደግሞ ያው ሀረግ ትልቅ ከሚለው ቅፅላዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮአል። ይህን በማድረጉ የተለየ ሀረግ አልፈጠረም። አሁንም የፈጠረው ስማዊ ሀረግ ነው። ርግጥ፣ የአሁኑ ሀረግ ከፊተኛው ሰፋ ይላል። ስለዚህም በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የይዘት ነው። በተራ ቁጥር (1) የሚታየው መዋቅር አንድ ስማዊ ሀረግ ከሆነ፣ ከእሱ ይሰፋል ያልነውና በተራ ቁጥር (10) የሚታየው መዋቅር ምን ሊባል ነው? ሀረግ ወይስ ከሀረግ በላይ የሆነ መዋቅር?


ቀደም ሲል፣ አንድ ሀረግ በመጠኑ ንዑስ ወይም አቢይ ሊሆን እንደሚችልና ይህንንም የሚወስነው በውስጡ የሚገኘው የተዋቃሪ ብዛትና ተግባር እንደሆነ ገልፀን ነበር። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ በተራ ቁጥር (1) የሚታየው መዋቅር አንድ አጃቢ ብቻ ስላለው፣ በተራ ቁጥር (10) ውስጥ ከሚገኘውና ሁለት አጃቢ ካለው መዋቅር በይዘቱ ያነሰ ነው። ስለዚህም ይህን መዋቅር ንዑስ ስማዊ ሀረግ ልንለው እንችላለን። ከእሱ የሚበልጠውንና በተራ ቁጥር (10) ውስጥ የሚገኘውን መዋቅር ደረጃ ለመወሰን፣ ተጨማሪ ምሳሌዎች ያስፈልጉናል። እስቲ የሚከተለውን እንመልከት።

የትናንቱ ትልቅ የሳር ቤት 11

ይህ መዋቅር በተራ ቁጥር (1)ም ሆነ በተራ ቁጥር (10) ውስጥ ከሚገኘው መዋቅር የሰፋ ነው። የሰፋበት ምክንያት መሪው ሶስት አጃቢዎች ስላሉት ነው። በዚህም ምክንያት መዋቅሩን አቢይ ስማዊ ሀረግ ልንለው እንችላለን። ይህን ስንል ግን፣ መዋቅሩ ከዚህ የበለጠ ሊሰፋ አይችልም ማለታችን አይደለም። ከዚህ የበለጠ ሊሰፋ ይችላል፤ ደረጃው ግን አሁንም ከአቢይ ሀረግ አያልፍም። እንዴት እንደሚሰፋ ከማየታችን በፊት በተራ ቁጥር (1፥ 10፥ እና 11) ውስጥ የሚታየውን የአጃቢዎችና የመሬ ቅንጅት ከሁለቱ የአቢይና የንዑስ ሀረግ ደረጃዎች አንፃር እንደገና እናጢነው።

በተራ ቁጥር (1) ውስጥ የሚገኘው መዋቅር ንዑስ ስማዊ ሀረግ ነው ካልን፣ በተራ ቁጥር (10) ውስጥ የሚገኘው መዋቅር ከዚህ ንዑስ ሀረግና ትልቅ ከሚለው ቅፅላዊ ሀረግ የተዋቀረ ነው፤ ለማለት ይቻላል። ይህም ማለት፣ ምሳሌ (10) ቤት ከሚለው መሬና የሳር እና ትልቅ ከሚሉት አጃቢዎች በአንድ ጊዜና በአንድ ደረጃ

የተዋቀረ ሳይሆን፣ መጀመሪያ <u>ቤት</u> የሚለው መሪና <u>የሳር</u> የሚለው አጃቢ ተዋቅረው በተራ ቁጥር (1) የሚታየውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ ከፈጠሩ በሁዋላ፣ በሁለተኛ ደረጃ ወይም ርከን ላይ <u>ትልቅ</u> የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ ከዚሁ ንዑስ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ በተራ ቁጥር (10) የሚታየውን ሰፋ ያለ መዋቅር ፈጥሮአል ማለት ነው። ከዚህ በሁዋላ ደግሞ ይኸው በተራ ቁጥር (10) ውስጥ የሚታየው ሀረግ፣ <u>የትናንቱ</u> ከሚለው ጊዜን አመልካች ሀረግ ጋር ተዋቅሮ በተራ ቁጥር (11) የሚታየውን በጣም ሰፊ የሆነ አቢይ ሀረግ ፈጥሮአል። በሌላ አነጋገር፣ አቢይ ሀረጉ በውስጡ ሁለት ሀረጎችን ይዞአል። እነሱም <u>የሳር ቤት</u> የሚለው ንዑስ ሀረግና <u>የትናንቱ</u> <u>ትልቅ የሳር ቤት</u> የሚለው አቢይ ሀረግ ናቸው። የንዑሱ ሀረግ መሪ <u>ቤት</u> የሚለው ስም እንደሆነ ሁሉ፣ የአቢይ ሀረጉ መሪ <u>የሳር ቤት</u> የሚለው ንዑስ ሀረግ ነው። ይህን የሁለቱን ሀረጎች የደረጃ ልዩነት እንደሚከተለው አድርጎ በዕፀ መዋቅር ማሳየት ይቻላል።




12

ከዕፀ-መዋቅሩ እንደምናየው፣ በመጀመሪያው ርከን ላይ <u>የሳር</u> እና <u>ቤት</u> ተዋቅረው [የሳር ቤት ] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ (ስሀ1) ፈጥረዋል። [የሳር ቤት] የሚለው ንዑስ ስማዊ ሀረግ የሆነበት ምክንያትም መሪው አንድ አጃቢ ብቻ ስላለው ነው። በሁለተኛው ርከን ላይ፣ ይህ ሀረግ <u>ትልቅ</u> ከሚለው አጃቢዎች ጋር ተዋቅሮ፣ [ ትልቅ የሳር ቤት ] የሚለውን ሰፊ ስማዊ ሀረግ (ስሀ2) ፈጥሮአል። ይህ አቢይ ስማዊ ሀረግ ነው። አቢይ የሚያሰኘው ከንዑሱ ስማዊ ሀረግ የበለጠ ሰፊ ይዘት ያለው መሆኑ

---

[2] የሀረጎችን ውስጣዊ አቀነጃጀት ከዚህ ላይ እንደሚታየው፣ በቅንፍ ወይም በዕፁ-መዋቅር ማመልከት ይቻላል። ዕፁ-መዋቅር የአቀነጃጀቱን ስርዓት በቀላሉ ስማየት ስለሚያስችል፣ ብዙ ጊዜ እሱን እንጠቀማለን፤ ምንም እንኳ ቦታ-ፈጅ ቢሆንም።

ነው። ንዑሱ ስማዊ ሀረግ የዚህ አቢይ ሀረግ አካልና መሪም ነው። ሀረጉ የትናንቱ ከሚለው የጊዜ ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ በርከን (3) ላይ እንደሚታየው ከሁሉም የሰፋ ሀረግ ሊሆን ችሎአል፡፡

ከዕፀ-መዋቅሩ እንደሚታየው፥ ጠቅላላ ሀረጉ ሶስት ርከኖች አሉት። እነሱም በቁጥሮቹ የተመለከቱት የንዑሱ ሀረግ (ስሀ1) የአቢዩ ሀረግ (ስሀ2) እና ስሀ(3) አንጉዋዎች ናቸው። በነዚህ ርከኖች ላይ የሚገኙት አጃቢዎችም የተለያዩ ናቸው። ልዩነታቸውም መሪውን ከሚገልፁበት ተግባር አኩዋያ ነው። በንዑስ ሀረጉ ርከን ውስጥ የሚገኘው የሳር የሚለው አጃቢ፣ የሀረጉ መሪ የሆነው፣ ቤት የሚለው ቃል የሚጠቁመው ነገር ከምን እንደ ተሰራ ያመለክታል። የሳር ቤት ስንል፣ ቤቱ ከሳር የተሰራ መሆኑን መግለፃችን ነው።

በሁለተኛው ርከን ላይ የሚገኘው ትልቅ የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ የሳሩ ቤት መጠን ምን ያህል እንደሆነ ይገልፃል። የመጀመሪያው አጃቢ ቤቱ የተሰራበትን ነገር ሲገልፅ፣ ሁለተኛው አጃቢ የቤቱን መጠን፣ ማለትም ትልቅነቱን፣ ይገልፃል። በሶስተኛው ርከን ላይ የሚገኘው የትናንቱ የሚለው ተጨማሪ አጃቢ ቤቱ የተሰራበትን ወይም የተገኘበትን ጊዜ ያመለክታል። ሶስቱም አጃቢዎች መሪውን ሰም ከተለያየ አንፃር ይገልፁታል ማለት ነው። በዚህም ምክንያት ሁሉም ገላጭ አጃቢዎች ናቸው።

መሪውን ከተለያየ አንፃር የሚገልፁ እንደመሆናቸው መጠን፣ አገባባቸውም እንደዚሁ በተለያየ ርከን ላይ ነው። መሪው ቃል የሚጠቁመው ነገር ከምን እንደተሰራ የሚገልፀው አጃቢ በመጀመሪያው ርከን፣ በንዑስ ሀረጉ ውስጥ፣ በቀጥታ ከመሪው ስም በስተግራ በኩል ተጠግቶ ሲገባ፣ መሪው የሚጠቁመውን ነገር መጠን የሚገልፀው ቅፅል በሁለተኛው ርከን ላይ፣ ጊዜውን የሚያመለክተው የትናንቱ የሚለው አጃቢም በሶስተኛው ርከን ላይ የሳር ቤት የሚለውን ንዑስ ሀረግ እየቀደመ ገብተዋል። በዚህ ደረጃ የትናንቱ ትልቅ የሳር ቤት የሚለው አቢይ ሀረግ መሪ ትልቅ የሳር ቤት የሚለው ሀረግ ነው። የዚህ ሀረግ መሪም የሳር ቤት የሚለው ንዑስ ሀረግ ነው። የአቢይ ሀረጉ መሪ ንዑስ ሀረግ ሲሆን፥ የንዑስ ሀረጉ መሪ ግን ሀረግ ሳይሆን ተራ ቃል ነው። ቃሉ ሌሎች ነገሮችን በየርከኑ እየጨመረ በማደግ መጀመሪያ ንዑስ፣ ከዚያ በየደረጃው እየሰፋ አቢይ ሀረግ ይሆናል። ከዚህ ላይ ባለፈው ንዑስ ክፍል ቃላት ሀረግ ይመዛሉ ያልነውን ያስታውሱ፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፥ ሀረጉ በተራ ቁጥር (11) ከሚታየው የበለጠ ሊሰፋ ይችላል። የሚሰፋውም የተለያዩ አጃቢዎችን በመጨመር ነው። ተጨማሪዎቹ አጃቢዎች የሚገቡት በተለያየ ርከን ላይ ነው። በመጀመሪያው ላይ የሚገባ ተጨማሪ አጃቢ የለም። ምክንያቱም በዚህ ደረጃ ሊገባ የሚችለው አጃቢ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ መሪው ቃል የሚጠቁመው ነገር የተሰራበትን ነገር የሚያመለክት አጃቢ ብቻ ነው። እንደዚህ ያለ አጃቢ ደግሞ ከአንድ በላይ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ምንም እንኩዋ አንዳንድ ነገሮች ከብዙ ነገር ሊሰሩ የሚችሉ ቢሆኑም፣ የሚጠቀሱት ከተሰሩባቸው ነገሮች በአንዱ ብቻ ስለሆነ ነው። ለምሳሌ፣ የሳር ቤት ስንል፣ ቤቱ ከሳር የተሰራ መሆኑን መግለፃችን ነው። ይሁን እንጅ፣ ቤቱ ከሳር ብቻ ሳይሆን፣ ከሌሎች ነገሮች ጭምር የተሰራ ሊሆን ይችላል። ቢሆንም፣ ከሁሉም ጎልቶ የሚታየው የቤቱ ጣሪያና ግድግዳ ስለሆነ፣ በዚሁ መሰረት ጣሪያው ወይም ግድግዳው የተሰራበትን ነገር በመጥቀስ፣ ጠቅላላ ቤቱን እንገልፃለን። የሳር ወይም የቆርቆሮ በማለት ክዳኑን፣ የእንጨት፣ የሸክላ፣ ወዘተ፣ በማለት ግድግዳውን እንጠቁማለን። ስለዚህም አንድን ቤት ስንገልፅ አትኩሮታችን ከነዚህ ከሁለቱ አያልፍም። በንዑስ ሀረግ ደረጃ ሊገባ የሚችለው አጃቢ አንድ ብቻ የሚሆነውም ከነዚህ

ከሁለቱ በአንዱ ብቻ ስለሚጠቀስ ነው። ሌሎች ነገሮችንም የምንገልፀው እንደዚሁ በአንዱ ባህሪያቸው ወይም አካላቸው ላይ በማተኮር ነው።

ሁለተኛው፣ በሶስተኛው፣ ወዘተ ርከን ላይ ግን ከላይ በተራ ቁጥር (11) እንደሚታየው፣ ከአንድ በላይ የሆኑ ገላጭ አጃቢዎች ሊገቡ ይችላሉ። ተግባራቸውም ንዑስ ሀረጉ የሚጠቁመው ነገር የሚገኝበትን ሁኔታ ወይም የተሰራበትን ቦታ፣ ጊዜ፣ ምክንያት፣ ዓላማ፣ መሳሪያ፣ ወዘተ፣ መግለፅ ነው። የሚከተለውን ተጨማሪ ምሳሌ እንመልከት።

የመርከቶው ትልቅ የሳር ቤት 13

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ የመርከቶው የሚለው ገላጭ አጃቢ፣ ትልቅ ከሚለው ቅፅል ቀድሞ ገብቶአል። ተግባሩም የሳር ቤት የሚለውን ንዑስ ሀረግ ከቦታ አንፃር መግለፅ ነው። የትናንቱ የሚለው የጊዜ ሀረግ በዚህ ምሳሌ ውስጥ ሊገባና ሀረጉን የበለጠ ሊያሰፋው ይችላል። አገባቡም ከዚህ ቀጥሎ እንደምናየው በሀረጉ መነሻ ላይ ነው።

(ሀ) የትናንቱ የመርከቶው ትልቅ የሳር ቤት 14
(ለ) ?የመርከቶው የትናንቱ ትልቅ የሳር ቤት
(ሐ) * የመርከቶው ትልቅ የትናንቱ የሳር ቤት

የእነዚህ ምሳሌዎች የተቀባይነት ደረጃ ከ(ሀ) ወደ (ለ) ከዚያም ወደ (ሐ) አሽቆልቁሎአል። ለዚህም ምክንያት የሆነው የትናንቱ የሚለው ገላጭ ሀረግ በ(ሀ) ውስጥ የሚገኝበትን ቦታ ትቶ፣ መጀመሪያ በ(ለ) ውስጥ ትልቅ ከሚለው ቅፅል በፊት፣ እንደገናም በ(ሐ) ውስጥ የሳር ከሚለው ስም በፊት መግባቱ ነው። ከዚህ የምንረዳው በአቢይ ሀረግ ውስጥ የሚገቡ ገላጮች ቅደም-ተከተልና ተዋረዳዊ ስርዓት የሚከተሉ መሆናቸውን ነው። ይኸውም የጊዜው ገላጭ ከቦታው፣ የቦታው ገላጭ ደግሞ ከቅፅሉ እየቀደመና ከፍ እያለ የሚገባ መሆኑ ነው። ይህ ቅደም-ተከተልና ተዋረዳዊ ስልፍ ሲፋለስ አረፍተ ነገሩ ይዛባል።

በዚሁ አይነት ሌሎች ገላጭ አጃቢዎችን እየጨመሩ ሀረጉን ማስፋትና በዚያም ውስጥ ቅደም-ተከተላዊ አገባባቸውን ማየት ይቻላል። ለተጨማሪ ማስረጃ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) የበርሜሉ ደረቅ የማር ጠጅ 15
(ለ) ? ደረቅ የበርሜሉ የማር ጠጅ
(ሐ) * ደረቅ የማር የበርሜሉ ጠጅ

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ የበርሜሉ የሚለው ስማዊ ገላጭ በመነሻ ላይ ይገኛል። በምሳሌ (ለ) ውስጥ ደግሞ በቅፅሉና የማር በሚለው ገላጭ መካከል ይገኛል። ስዚህም ምክንያት የሀረጉ ተቀባይነት አጠያያቂ ሆኖአል። በምሳሌ (ሐ) ውስጥ ደግሞ ጠጅ ከሚለው መሪ ስም ቀድሞ በመግባቱ አረፍተ ነገሩ ተዛብቶአል።

በነዚህና በተራ ቁጥር (12) ውስጥ በአቢዩ ሀረግ ርከን ላይ የሚገኙ ስማዊ ገላጮች ቦታቸውን እየለቀቁ ወደ ንዑሱ ሀረግ በተጠጉ ቁጥር፣ የሀረጎቹ ተቀባይነት እየቀነሰ እንደሚሄድ አይተናል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በንዑስ ሀረግ ርከን ላይ መገኘት ያለበት ገላጭ ቦታውን ለቆ ወደ አቢይ ሀረጉ ርከን ሲጠጋ፣ የአረፍተ ነገር መዛባትን ሊያስከትል ይችላል። ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት።

16


(ሀ) የተዝካሩ ደረቅ የማር ጠጅ
(ለ) ? የተዝካሩ የማር ደረቅ ጠጅ
(መ) * የማር የተዝካሩ ደረቅ ጠጅ

የማር የሚለው ለማዊ ገላጭ መሰረታዊ ቦታው በምሳሌ (ሀ) ውስጥ እንደሚታየው፣ ጠጅ ከሚለው መሪ ስም በፊት ነው። በዚህ ቦታ ተገኝቶ መሪውን ስም በማጀብ ንዑሱን ሀረግ ይመሰርታል። ይህን ቦታውን በመልቀቅ ከመሪው እየራቀ በሄደ ቁጥር፣ የሀረጉ የተቀባይነት ደረጃ እየቀነሰ ይሄዳል። ከዚህም ሁኔታ በመሪውና የማር በሚለው ገላጭ ስም መካከል ጥብቅ ግንኙነት እንዳለ መረዳት ይቻላል።

እስካሁን ካየናቸው ምሳሌዎች እንደምንረዳው፣ በአቢይ ሀረግ ውስጥ የሚገኙ አጃቢዎች ሁለት አይነት ናቸው። እነሱም ለሞችና ቅፅሎች ናቸው። ለሞቹን በጥቅሉ ተውሳከ ለሞች ልንላቸው እንችላለን። ትርጉሙ የስም ጭማሪዎች ማለት ነው። ጭማሪነታቸው ከነሱ ቀጥሎ ለሚገኘው ሀረግ ነው። ተውሳከ ለሞች የሚባሉበት ምክንያት ከንዑሱ ለማዊ ሀረግ ላይ እየተጨመሩ ሀረጉን ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከምክንያት፣ ወዘተ፣ አኳዋያ ስለሚገልፁትና ስለሚያስፉት ነው።

በንዑሱ ሀረግ ውስጥ የሚገኘውን አጃቢ ለማዊ ልንለው እንችላለን። መሪው ስም የሚጠቁመው ነገር የተሰራበትን ወይም የተገኘበትን፣ ማለትም ምንጩን፣ ስለሚጠቁም ነው። ለምሳሌ የማር ጠጅ በንል፣ የማር የሚለው ሀረግ ጠጁ የተጠመቀበትን (የተጣለበትን) ነገር ይገልፃል። የጎጃም የማር ጠጅ ስንል ደግሞ የጎጃም የሚለው የማሩ ጠጅ የመጣበትን ወይም የተጠመቀበትን ቦታ ይገልፃል። ስለዚህም የጎጃም የሚለው ተውሳከ ለማዊ ገላጭ ሲሆን፣ የማር የሚለው ለማዊ ገላጭ ነው። ለማዊ ገላጮችን መሙሊያ በማለት፣ ከተውሳከ ለማዊ ገላጮች ልንለያቸው እንችላለን። ከዚህ አኳዋያ በአቢይ ሀረግ ስር የሚገኙ ተዋቀሪዎችን በጥቅሉ ገላጭ፣ በንዑስ ሀረግ ስር የሚገኙትን ደግሞ መሙሊያ ብሎ መለየት ይቻላል። ርከናቸውንም በዕዐ-መዋቀር እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

17




ከመሙሊያውና ከመሪው የተዋቀረውን ንዑስ ሀረግ (ስሀ1) ወደ አቢይ ሀረግነት የሚያሳድገው ልዩ ልዩ ገላጭ ተዋቃሪ ነው። ስለሆነም በየርከኑ ላይ የሚገኝ ማንኛውም ገላጭ አጎላማሽ (አሳዳጊ) ይባላል። ስለ መሪው የተለያየ ተጨማሪ መረጃ

አየሰጠ የሚያጅብና የሚያሰፋ እናም የሚያጎላምስ መዋቅር ነው። ርከኑም በሶስት ብቻ ሳይወሰን ይችላል፡፡ የኮከብ ምልክትዋ (*) የምታመለክተውም ይህን ሁኔታ ነው፡፡

በተራ ቁጥር (12) ከሚታየው ዕፀ-መዋቅር ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ ተዋቃሪዎቹ በሙሉ ተራ ቃላት ይመስላሉ። ይህ ግን ትክክል አይደለም፤ ምክንያቱም መሪው ስም ብቻ ነው፣ ተራ ቃል ሊሆን የሚችለውና የየሀረጉ ዘር በመሆንም አይነቱን የሚወስነው። መሪው ቃል ስም ከሆነ፣ ሀረጉ ስማዊ ይሆናል። መሪው ቃል ቅፅል ከሆነም፣ ሀረጉም እንደዚሁ ቅፅላዊ ይሆናል፣ ወዘተ። የሀረጉ አይነት በመሪው ቃል ክፍል እንደሚወሰን ሁሉ፣ ሀረጋዊ ሰፋቱ፣ ይዘቱ ብሎም ርከኑ በተዋቃሪዎቹ ሀረጎች ይወሰናል። ስለዚህም ከመሪው ጋር የሚዋቀሩት ክፍሎች በሙሉ ሀረጎች ናቸው። ባጭሩ አንድ ሀረግ አይነቱን ከመሪው፣ ሀረጋዊ ደረጃውን ከተዋቃሪ መሙሊያዎችና አጎላማሽ ሀረጎች ያገኛል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

እስካሁን የተመለከትነው አንድ ስም ከአንድ መሙሊያና ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ አጎላማሾች ጋር በተዋረድ እየተዋቀረ ንዑስና አቢይ ስማዊ ሀረግን ሊመስርት ነው። ከስሙ ጋር የሚዋቀሩት ሀረጎች በነዚህ ብቻ የተወሰኑ አይደሉም። ከአቢይ ሀረጉ ጋር እየተዋቀሩ ይህንኑ ሀረግ ወደ ከፍተኛ አቢይ ሀረግ ሊያሳድጉ የሚችሉ ሌሎች መዋቅሮች አሉ። እነዚህም ባለፈው ክፍል ያየናቸውና መስተዓምር ያልናቸው ክፍሎች ናቸው። አገባባቸው በየሀረጉ መነሻና አንዳንድ ጊዜም በመድረሻው ላይ ነው። ዝርዘሩን ቆየት ብለን እናየዋለን፡፡ ለጊዘየው የሚከተሉትን ለእብነት እንመልከት።

(ሀ) _ያ_ ጎበዝ የሰዋሰው መምህር 18


(ለ) _አንድ_ የጎጃም የቅኔ መምህር

(መ) የ_እኛ_ የእንግሊዝኛ መፅሀፍ

(ሰ) የእንግሊዝኛ-ው መፅሀፍ

የመስተዓምሮች ተግባር አቢይ ሰማዊ ሀረጎች የሚገልፁዋቸውን ነገሮች መወሰን ነው። እወሳሰኑም ነገሮቹ ከሚገኙበት ቦታ፣ ከመጠናቸውና ከገንዘቢያቸው (ባለቤታቸው) እና ከዚህ በፊት የተጠቀሱና ስለዚህም የታወቁ ከመሆናቸው ወይም ካለመሆናቸው አኳዋያ ነው። በዚሁ መሰረት ጠቋዋሚ፣ መጣኝ፣ አገናዛቢ እና ዕምር (የታወቁ) መስተዓምሮች እንደሚባሉ ባለፈው ክፍል ተገልፆአል። ከነዚህ መካከል የዕምርነቱ ምዕላድ በመሪው ቃል ወይም በአጎላማሹ መድረሻ ላይ ይገኛል፡፡ የሀረጎቹ ወርዳዊ (ቅደም-ተከተላዊ) አቀማመጥ በምሳሌ (ሀ) እንደሚታየው ሲሆን፣ ተዋረዳዊ አቀማመጣቸው ደግሞ ከዚህ በታች እንደተመለከተው ነው።

19




ከዕፀ-መዋቅሩ እንደሚታየው፣ መበተዓምሩ ያ የተዋቀረው ከስማዊ ሀረግ (ስሀ2) ጋር ነው። ተግባሩም ይህ ስማዊ ሀረግ፣ ማስትም ጎበዝ የበዋበው መምሀር የሚለው ከፍል፣ የሚጠቁመውን ነገር የትነት መወሰን ነው። እንደዚያ እያደረገ ሀረጉን ወደ ከፍተኛ አቢይ ሀረግ (ሰሀ3) ያሳድገዋል።

ዐበቱ የመበተዓምር አይነቶች ተከታትለው ሲመጡና በማዊ ሀረጉን (በሀ2)ን ሲወበኑ ይችላሉ። የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው።

(ሀ) እነዚያ የእኔ ሁለት [የሰዋሰው መፃሀፍት] 20
(ለ) ? የእኔ እነዚያ ሁለት [የሰዋበው መፃህፍት]
(መ) ? ሁለት የእኔ እነዚያ [የሰዋበው መፃህፍት]


መስተዓምሮቹ የሚወስኑት በቅንፉ ውስጥ የሚታየውን አቢይ ስማዊ ሀረግ ነው። መሰረታዊ ቅደም-ተከተላዊ ብሎም ተዋረዳዊ አገባባቸውም በምሳሌ (ሀ) እንደሚታየው፣ ጠቋሚው ቀድሞ፣ አገናባቢው እሱን ተከትሎ፣ መጣኙ ደግሞ ዐበተኛ ሆኖ በመሰለፍ ነው። ይህ አገባብ ቢፋለስ፣ ውጤቱ በምሳሌ (ለ) እና (መ) እንደሚታየው ያለ መዛባት ይከሰታል። ይህን ቅደም-ተከተላዊ በርዓት እንደሚከተለው እናሳያለን።

³ መስተዓምሮችም የራሳቸውን ሀረግ ይመሰርታሉ። እንዴት እንደሚመሰርቱ ቆይተን እንመለከታለን።

[ጠቋሚ - አገናዛቢ- መጣኝ - ስሀ 21

አንድ ንዑስ ስማዊ ሀረግ በተለያዩ አጎላማሾች ሊገለፅ እንደሚችል ሁሉ፣ አንድ አቢይ ስማዊ ሀረግም በተለያዩ መስተዓምሮች ሊወሰን እንደሚችል ከምሳሌ 20(ሀ) መረዳት ይቻላል። ከዚህ አንፃር፣ ከአንድ መሙሊያ ሀረግ ጋር ብቻ የሚዋቀረው ቃላዊ የሆነው መሪ ስም ብቻ ነው። ይህን በየርከኑ ሊገኝ የሚችለውን የተዋቃሪ መጠን በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው አጠቃሎ ማሳየት ይቻላል።

22




እንግዲህ እስካሁን በዝርዝር ያየነውን ጠቅለል ብናደርገው፣ አንድ ስማዊ ሀረግ የአራት ነገሮች ቅንጅት ነው፣ ለማለት እንችላለን። እነሱም ከዚህ ዕፀ-መዋቅር እንደሚታየው፣ መሪ፣ መሙሊያ፣ አጎላማሽና መስተዓምር ናቸው። አወቃቀራቸው ወርዳዊና ተዋረዳዊ ነው፡፡ መሪው ቃልና መሙሊያው ሀረግ በአንድ ወርድ ወይም ርከን ላይ ይገኛሉ፡፡ አጎላማሹና ንዑሱ ስማዊ ሀረግ (ስሀ1) እንደዚሁ በሁለተኛው ርከን በቅደም-ተከተል ይገኛሉ፡፡ በመጨረሻም መስተዓምሩና አቢዩ ስማዊ ሀረግ (ስሀ2) በሶስተኛው ርከን ላይ እንደዚሁ በቅደም-ተከተል ተሰልፈዋል፡፡ ይህ አይነተኛ የመዋቅር ባህሪ ነው፡፡ ባህሪነቱ ግን የቁዋንቁዋ ብቻ ሳይሆን፣ የየቁዋንቁዋው ተናጋሪ ማህበረ-ሰብም ጭምር ነው፡፡ ያልተዋቀረ የማህበረሰብ አባል የትም የለም፡፡ መዋቅሩ የዕድር፣ የፖለቲካ፣ የማህበር፣ ወዘተ፣ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም ውስጥ መሪና ተመሪ አለ፡፡ እነዚህ ደግሞ በአንድ የስልጣን ርከን ላይ አይቀመጡም፡፡ ፕሮቶኮሉ አይፈቅድም፡፡ ወደ ጉዳያችን እንመለስ፡፡

ከላይ በዕፀ መዋቅሩ ውስጥ የሚታየው መዋቅራዊ ተዛምዶ መሙሊያ ያላቸውን፣ እንደ ጠጅ ያሉ ስሞችን ሀረግ መሰረት ያደረገ ነው። እንደነዚህ ያሉ ስሞች ባለመሙሊያ ስሞች ሊባሉ ይችላሉ። ይህ ደግሞ መሙሊያ የሌላቸው ስሞች

---

[4] ይህ የኮከብ ምልክት የአጎላማሾችና የመስተዓምሮች ቁጥር ከአንድ በላይ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል።


[5] ከፍተኛ አቢይ ሀረጎችን በአሀዝ አናመለክትም። ተራ አቢይ ሀረጎችን በሁለት ቁጥር፣ ንዑስ ሀረጎችን በአንድ ቁጥር እናመለክታለን። በገሀድ የሚታይ ገላጭ ወይም መሙሊያ የሌለው፣ ማንኛውም አቢይ ሀረግ በዕፀ-መዋቅር ላይ በቁጥር ላይመለከት ይችላል።

አሉ እንዴ? የሚል ጥያቄን ያስነሳል። ርግጥ ነው፣ የዚህ አይነት ስሞች አሉ። ስለዚህም ስሞችን መሙሊያ ያላቸውና የሌላቸው ብሎ በሁለት መመደብ ይቻላል። ሁኔታው ግን በስሞች ብቻ የሚወሰን አይደለም፤ ሌሎች የቃላት ክፍሎችንም ያጠቃልላል። ዝርዝሩን ወደፊት እናየዋለን። አሁን መሙሊያ ወደሌላቸው ሀረጎች እንሂድና ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት።

23
(ሀ) ያች የምስራቅ ኮከብ
(ለ) ያች የንጋት ጨረቃ
(መ) የገና ጀንበር
(ሰ) የጥቅምት ውርጭ

የእነዚህ ሀረጎች መሪ ስሞች <u>ኮከብ</u>፣ <u>ጨረቃ</u>፣ <u>ጀንበር</u> እና <u>ውርጭ</u> የሚሉት ስሞች ናቸው። ከእነዚህ ጋር የተዋቀሩት ጊዜንና ቦታን የሚያመለክቱ ተውሳከ ስማዊ ገላጮችና መስተዓምሮች ናቸው። ተግባራቸውም እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ አንድን ንዑስ ሀረግ ማጎላመስና መወሰን ነው። የየምሳሌዎቹ ንዑስ ሀረግ የተመሰረተው በመሪው ስም ብቻ ነው። ለዚህ ምክንያቱ መሪው ስም የሚጠቁመው ነገር የተሰራበትን ነገር የሚገልፅ ሀረግ አለመኖሩና ሊኖርም አለመቻሉ ነው። <u>ቤት</u> ከምን እንደሚሰራ የሚታወቀውን ያህል፣ ኮከብ ከምን እንደሚፈጠር ቢያንስ ለተራው የቋንቋዋ ተጠቃሚ ዕውቅ አይደለም። ስለዚህም እንደ <u>ኮከብ</u> ያሉ ስሞች ገላጭ እንጅ መሙሊያ ሀረግ የላቸውም። በዚህ መሰረት የምሳሌ 23(ሀ) መዋቅር የሚከተለውን ይመስላል።

24




<u>ኮከብ</u> የሚለው መሪ ስም መሙሊያ ስለሌለው፣ ንዑሱን ስማዊ ሀረግ (ስሀ1) የመሰረተው ብቻውን ነው። አቢዩን ስማዊ ሀረግ (ስሀ2) ግን <u>የምስራቅ</u> ከሚለው ገላጭ ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ መስርቶአል። ይህ ደግሞ በተራው <u>ያች</u> ከሚለው ጠቋሚ መስተዓምራዊ ሀረግ ጋር በመቀናጀት ዋናውን ሀረግ ሊመሰርት ችሎአል።

እንደ ኮከብና ጠጅ ባሉ ስሞች መካከል ያለው መዋቅራዊ ልዩነት በንዑስ ሀረግ ደረጃ ብቻ ነው። ይኸውም እንደ ጠጅ ያሉት፣ ከፍ ሲል እንዳየነው፣ መመሚያ ሲኖራቸው፣ እንደ ኮከብ ያሉት የሌላቸው መሆኑ ነው። ከዚያ ውጭ ሁሉም ከገላጮችና ከመስተዓምሮች ጋር እየተዋቀሩ አቢይ ሀረጋቸውን ስለሚመሰርቱ በመካከላቸው ልዩነት የለም።

እስካሁን ያየነው የነባር ስሞችን ሀረግ አወቃቀር ነው። ከዚህ ቀጥለን የውልድ ስሞችን ባህሪ እንመለከታለን። በክፍል ሁለት እንዳየነው፣ ውልድ ስሞች የሚባሉት ከነባር ስሞች፣ ቅፅሎችና ከስሮች ላይ በመስራች ምዕላድ አማካኝነት የሚፈጠሩ ናቸው። የነዚህ አይነት ስሞች የሀረግ አወቃቀር ባህሪ ከሚወለዱበት ቃል ያወቃቀር ባህሪ ጋር ተመሳሳይ ነው። ምንጩ ቃል መመሚያ የሚይዝ ከሆነ፣ ውልዱ ቃልም እንደዚሁ መመሚያ ይይዛል። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ዜማ ደረሰ 25
(ለ) ያ የዜማ ደራሲ
(መ) ያ የዜማ ድርሰት

የነዚህ ሀረጎች መሪዎች የተሰመረባቸው ቃላት ናቸው። ሁሉም ውልድ ሲሆኑ፣ እወላለዳቸው /ድ-ር-ስ/ የሚለውን ስር መሰረት ያደረገ ነው። ይህ ስር ደግሞ መመሚያ ሰማዊ ሀረግ ይፈልጋል። የእሱ ውልድ የሆኑት ደረሰ፣ ደራሲ እና ድርሰትም እንደዚሁ መመሚያ ሰማዊ ሀረግ ይፈልጋሉ። በግሱና በስሞቹ መካከል ያለው ልዩነት፣ ግሱ መመሚያዎቹን የግድ ሲፈልግ፣ ስሞቹ ግን የግድ የማይፈልጉ መሆናቸው ነው። በሌላ አነጋገር፣ ስሞቹ ያለመመሚያቸው ሀረጉን እንደሚከተለው ሊመሰርቱ ይችላሉ።

(ሀ) ያ [ ] ደራሲ 26
(ለ) ያ [ ] ድርሰት
(መ) ? ካሳ [ ] ደረሰ

ቅንፎቹ ዜማ የሚለውን መመሚያ ቦታ ያመለክታሉ። መመሚያው በምሳሌ (ሀ) እና (ለ) ቢገደፍም፣ የምሳሌዎቹ ተቀባይነት አልቀነሰም። የምሳሌ (መ) ተቀባይነት ግን ጥያቄ ውስጥ ገብቶአል። ለዚህ ምክንያቱ የመመሚያው መገደፍ ነው። ይህም እንደ ደረሰ ያሉ ግሶች ያለመመሚያቸው ሊቆሙ እንደማይችሉ ያሳያል። ዋናው ቁም ነገር፣ ከአንድ ዘር የሚፈጠሩ ቃላት የሀረግ አወቃቀር ባህሪ ሊወራረሱ የሚችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ነው።

ስለ ስማዊ ሀረግ እስካሁን በዝርዝር ያየነውን እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል። ማንኛውም ስማዊ ሀረግ ከመሪ ስም፣ ከመመሚያ፣ ከተለያዩ ገላጮች እና ከመስተዓምሮች ይመሰረታል። መሪው ስም ከመመሚያው ጋር ተቀናጅቶ ንዑሱን ሀረግ ይመሰርታል። ይህ ሀረግ ደግሞ ከቅፅላዊና ከተውሳከ ስማዊ ሀረጎች ጋር በተዋረድ እየተዋቀረ አቢዩን ስማዊ ሀረግ ይመሰርታል። ይህም አቢይ ሀረግ ከመስተዓምሮች ጋር በመቀናጀት ዋናውን ስማዊ ሀረግ ይፈጥራል። መሪው ስም

ሊዋቀር የሚችለው ከአንድ መሙሊያ ሀረግ ጋር ብቻ ነው። ይህም መሙሊያ መሪው ቃል የሚጠቁመው ነገር የተሰራበትን ነገር የሚያመለክት ነው። ከእቢዩ ሀረግ ጋር የሚዋቀሩት መስተዓምሮች ሶስት አይነት ናቸው። እነሱም ጠቋዋሚ፣ አገናዛቢና መጣኝ ይባላሉ። ጠቋዋሚው የትነቱን፣ አገናዛቢው የማንነቱን፣ መጣኙ ደግሞ መጠኑን ይወበናል። የንዑሱ ሀረግ መሪ በም ተራ ቃል ነው። ሀረግ ሊሆን የሚችለው በየርከኑ ከመሙሊያና ከገላጭ ሀረግ ጋር በለሚዋቀር ነው። ከየተዋቃሪው ሀረግ ሀረጋዊነትን፣ ከመሪው በም በማዊነትን ያገኛል። ስሞች መሙሊያ በመያዝና ባለመያዝ በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። መሙሊያ የማይዙት ንዑለ ሀረጋቸውን በመሪው ስም አማካኝነት ብቻ ይመሰርታሉ። በሌላ በኩል ደግሞ መሪ ስሞች ነባርና ውልድ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ውልድ የሆኑት የተወሰዱበትን ቃል መዋቅራዊ ባህሪ ይወበዳሉ። ቃሉ መሙሊያ የሚወሰድ ከሆነ፣ እነሱም መሙሊያ ይወበዳሉ። በዚህም ይህን ንዑብ ክፍል ለጊዜው እንቋዋጫለን። ለጊዜው የምንልበት ምክንያት ወደፊት በሊላ ክፍል ስለምንመለበበት ነው።

## *ግሳዊ ሀረግ*

ባለፈው ንዑስ ክፍል በሞች ከበማዊ መሙሊያ ሀረግ፣ ከተውሳከ ሰማዊና ቅፅላዊ አኀላማሽ ሀረጎች እንዲሁም ከሶበት አይነት መበተዓምሮች ጋር በየደረጃው እየተዋቀሩ ንዑስና እቢይ በማዊ ሀረጎችን ሊመሰርቱ ተመልክተናል። በዚህ ንዑስ ክፍል፣ ግሶች ልክ እንደ በሞች ከመሙሊያዎች፣ ከአኀላማሾችና ከመበተዓምሮች ጋር እየተዋቀሩ ንዑስና እቢይ ሀረጋቸውን እንዴት እንደሚመሰርቱ እናያለን።

ይህን ለማድረግ ቀና ይሆን ዘንድ፣ ግሶችን በአይነት በአይነታቸው እንከፋፍላቸዋለን። ከትርጉም አንፃር ሊታዩ፣ ግሶች የሁነትና የድርጊት ተብለው በሁለት ብቻ ሊከፈሉ ይችላሉ። የድርጊት የሚባሉት አንድ ሰው የሚፈፅመውን ተግባር የሚገልፁ ናቸው። መጀመሪያ የሚከተሉትን የድርጊት ግሶች እንይ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጠጣ | መጣ | ሄደ | 1 |
| ጠረገ | ሰበረ | ቀደደ | |

የድርጊት ግሶች ባለቤት አድራጊ፣ ማለትም የድርጊቱ ፈፃሚ ነው። ለምሳሌ፣

ካሳ ብርጭቆ ሰበረ 2

በንል፣ ካሳ የሚለው በም የድርጊቱ ፈፃሚ ባለቤት መሆኑን መግለፃችን ነው። ድርጊቱ የተፈፀመው በብርጭቆ ላይ ነው። በለዚህም ብርጭቆ ተደራጊ ወይም ድርጊት ተቀባይ ስም ነው።

የሁነት ግሶች የሚባሉት፣ አንድ ሰው የሚፈፅመውን ድርጊት ሳይሆን፣ እሱ ራሱ የሚሆነውን ነገር ወይም የሚገኝበትን ሁኔታ እንዲሁም፣ የሚያሳየውን ባህሪ የሚገልፁ ናቸው። የሚከተሉት የእነዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሆነ | ወፈረ | አፀነ | 3 |
| ከሳ | ቀጠነ | ፈዘዘ | |

የእነዚህ አይነት ግሶች ባለቤት ሁዋኝ ስም ነው። አድራጊ አይደለም፡፡ ለምሳሌ፣

ካሳ አስተማሪ ሆነ 4

ስንል፣ የምንገልፀው የካሳን አስተማሪ የመሆን ነገር ነው። በዚህም ካሳ አስተማሪ ካለመሆን አስተማሪ ወደ መሆን መለወጡን እንረዳለን። ካሳ ወፈረ ስንልም፣ ካለመወፈር ወደ መወፈር መለወጡን እንገነዘባለን። ግሶቹ የሚገልፁት ድርጊትን ሳይሆን፣ ለውጥን ነው። ባለቤታቸውም የለውጡ ተቀባይ ወይም ተለዋጭ ነው።

ከመዋቅራዊ ባህሪ አኳዋያ ሲታዩ፣ የድርጊትና የሁነት ግሶች የተለያዩ ናቸው። የድርጊት ግሶች ከሚገልፁት ድርጊት ጋር የሚዛመድ መሙሊያ አላቸው። የሁነት ግሶች ግን አንድም መሙሊያ የላቸውም፣ ካላቸውም ከሁኔታው ጋር ሳይሆን፣ ከሁዋኙ ባለቤት ጋር የተገናዘበ ነው። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ብርቱካን በላ 5
(ለ) ካሳ ገበሬ ሆነ

በላ የሚለው የድርጊት ግስ መሙሊያ ብርቱካን የሚለው ስም ነው። ይህ ስም የድርጊቱ ተጠቂ (ተደራጊ) ነው። ከካሳ ጋር ያለው ግንኙነት የአድራጊና የተደራጊነት ነው። በምሳሌ (ለ) ውስጥ ገበሬ የሚለው ስም ሆነ የሚለው ግስ መሙሊያ ነው። ከካሳ ጋር ያለው ግንኙነትም የእኩነት ነው። ሁለቱም የሚጠቁሙት አንድን ነገር ነው። ገበሬው ካሳ ነው፤ ካሳም ገበሬው ነው። በሁለቱ መካከል ልዩነት የለም፡፡

በድርጊትና በሁነት ግሶች መካከል ያለው ሌላው መዋቅራዊ ልዩነት የሚወስዱት የመሙሊያ መጠን ነው። የድርጊት ግሶች አንድ ወይም ሁለት መሙሊያ ሊኖራቸው ይችላል። የሁነት ግሶች መሙሊያ አንድ ብቻ ነው፡፡ እሱም ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ራሱ ሁዋኙ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [ለአስቴር ገንዘብ ሰጣት] 6
(ለ) ካሳ [ምሳውን በላ]
(መ) ካሳ [ወታደር መሰለ]
(ሰ) ካሳ [ከሳ]

ሰጣት የሚለው የድርጊት ግስ ነው። ሁለት መሙሊያዎች አሉት። እነዚህም የተሰመረባቸው ስሞች ናቸው። በላ የሚለውም እንደዚሁ የድርጊት ግስ ነው። ይሁን እንጅ መሙሊያው አንድ ስም ብቻ ነው። እሱም ምሳውን የሚለው ስም ነው፡፡ መሰለ የሚለው ደግሞ የሁነት ግስ ሲሆን፣ እሱም በላ እንደሚለው ግስ ባለአንድ መሙሊያ ነው። መሙሊያውም ወታደር የሚለው ስም ነው፡፡ በመጨረሻም ከሳ የሚለው ግስ አለ። ይህም እንደ መሰለ የሁነት ግስ ነው። ይሁን እንጅ፣ መሙሊያ የለውም[6]። በጥቅሉ ግሶችን እንደ መሙሊያቸው አይነትና መጠን መከፋፈል ይቻላል። ከዚህ ቀጥለን የምናሳየው የሀረግ አወቃቀር ይህንን ልዩነት መሰረት ያደረገ ነው።


[6] ከዚህ ላይም ካሳ ራሱ መሙሊያ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ነገር ላለማከበድ ወደ ዝርዝሩ አንገባም፡፡

## *ኢ-ሳቢ ግሳዊ ሀረግ*

ከፍ ሲል ለመጠቆም እንደሞከርነው፣ ግሶች መሙሊያ ያላቸውና የሌላቸው ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። መሙሊያ ያላቸው ደግሞ እንደ መሙሊያው ብዛት ባለአንድ ወይም ባለሁለት መሙሊያ እየተባሉ ሊለዩ ይችላሉ። በተጨማሪም እንደ መሙሊያቸው አይነት በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። ይኸውም መሙሊያቸው ተደራጊ ስማዊ ሀረግ የሆኑና መሙሊያቸው ተደራጊ ስማዊ ሀረግ ያልሆኑ ብሉ በመለየት ነው። መሙሊያቸው ተደራጊ ስማዊ ሀረግ የሆኑት ሳቢ ግሶች ሲባሉ፣ መሙሊያቸውም ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ይባላል። መሙሊያ የሌላቸው ወይም መሙሊያቸው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ያልሆነ ግሶች በጥቅሉ ኢ-ሳቢ ግሶች ይባላሉ። ሀረጉም ኢ-ሳቢ ግሳዊ ሀረግ ይባላል። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [ ደነገጠ ] 1
(ለ) ካሳ [ ወደ ጎንደር ሄደ ]

በመጀመሪያው ምሳሌ ደነገጠ የሚለው የሁነት ግስ መሙሊያ የለውም። ስለዚህም የተዋቀረው ከደንጋጩ ባለቤት ከካሳ ጋር ብቻ ነው። በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ፣ ሄደ የሚለው የድርጊት ግስ ወደ ጎንደር ከሚለው መሙሊያ ሀረግ ጋር ተዋቅሯል። መሙሊያው የጉዞውን ድርጊት መድረሻ ያመለክታል። የመድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። የሁለቱን ግሶች ንዑስ ሀረግ አወቃቀር በዛፍ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።



2


በግልፅ እንደሚታየው፣ ሁለቱ ግሶች የሚለያዩት መሙሊያ በመያዝና ባለመያዝ ነው። ይህ ልዩነት ግን በንዑስ ሀረግ ደረጃ ብቻ ነው። ሁለቱም አቢይ ሀረጋቸውን ከተለያዩ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር በመቀናጀት እንደሚከተለው ይመሰርታሉ።

(ሀ) [[በድንገት] [ወደ ጎንደር ሄደ ] ] 3
(ለ) [[በሀይል] [ደነገጠ ] ]

---

[7] መስተዋድዳዊ ሀረጎችን በ*ጎን-ጎልስ* መልክ ያስቀመጥናቸው፣ ውስጣዊ አቀነጃጀታቸው ያልታየ መሆኑን ለመጠቆም ነው። ወደፊትም ሌሎች ያልተተነተኑ ሀረጎችን የምናሳየው በዚሁ መልክ መሆኑን ከወዲሁ እናስገነዝባለን።

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ <u>በድንገት</u> የሚለው ቅንጅት መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፣ ተግባሩ <u>ወደ ጎንደር ሄደ</u> የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መግለፅ ነው። አገላለፁም የአካሄዱን ሁኔታ በመወሰን ነው። በምሳሌ (ለ) ውስጥም <u>በሀይል</u> የሚለው እንደዚሁ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፥ ተግባሩ የድንጋጤውን ደረጃ መግለፅ ነው። ሁለቱ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ገላጭ አጎላማሾች ሲሆኑ፣ ሁለቱ ንዑስ ሀረጎች ደግሞ ተገላጭ መሪዎች ናቸው። ከላይ በቅንፍ የሚታየውን የገላጭና የመሪ አቀማመጥ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ምሳሌ (ሀ)ን ብቻ በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።




4

በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>ወደ ጎንደር</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ የግሱ መሙሊያ ሆኖ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1)ን መሰርቶአል። <u>በድንገት</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግም የንዑሱ ሀረግ ገላጭ ሆኖ በመግባት አቢዩን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) አዋቅሮአል። ይህ አቢይ ሀረግ ተጨማሪ ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን ሊይዝ ይችላል። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) [ [ትናንት] [በድንገት] [በመኪና] [ወደ ጎንደር ሄደ]] 5
(ለ) [ [በድንገት] [ትናንት] [በመኪና] [ወደ ጎንደር ሄደ]]
(መ) [ [በመኪና] [ትናንት] [በድንገት] [ወደ ጎንደር ሄደ]]


ትናንት፣ <u>በድንገት</u>ና <u>በመኪና</u> የሚሉት ሀረጎች <u>ወደ ጎንደር ሄደ</u> የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ከጊዜ፣ ከሁኔታና ከማድረጊያ አኳዋያ ይገልፁታል። ቅደም-ተከተላቸውም ሊቀያየር ይችላል። ይህም ሀረጎቹ በተመሳሳይ ርከንና ተግባር ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ያመለክታል። ርከናቸው አቢዩ ሀረግ ሲሆን፣ ተግባራቸው ገላጭነት ነው። ገላጭነታቸውም ለንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ነው። ይህም በስማዊ ሀረጎች ላይ ያየነውን ሁኔታ ሊያስታውሰን ይገባል።

አንደ ምሳሌ 5(ሀ) ያሉ አቢይ ግሳዊ ሀረጎች ከመጣኝ መስተዓምር ጋር በመዋቀር ዋናውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ እንደሚከተለው ይመሰርታሉ።

[ [እንዴ][ [በድንገት] [ወደ ጎንደር ሄደ] ] ] 6

እንዴ የሚለው መጣኝ መስተዓምር በድንገት ወደ ጎንደር የመሄዱ ተግባር በንት ጊዜ እንደ ተፈፀመ ይገልፃል። ዕፀ-መዋቅራዊ ቅርፁን እንደሚከተለው እናሳያለን።

7




ወደ ጎንደር የሚለው መድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግ መሙሊያ በስሆን፣ ከመሪው ግስ ጋር ተዋቅሮ፣ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) መስርቶአል። በድንገት የሚለው ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረግ ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ጋር ተቀናጅቶ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) አዋቅሮአል። ይህ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ከመጣኙ መስተዓምር ጋር ሆኖ ዋናውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ)ን መሰርቶአል።

ይህ እንግዲህ በንዑስ ሀረግ ውስጥ የግሱንና የመሙሊያውን፣ በአቢይ ሀረግ ውስጥ የንዑሱን ሀረግና የአጎላማሾቹን፣ እንዲሁም የዚህን አቢይ ሀረግና የመስተ- ዓምሩን አገባብ በተመለከተ የተነነብነው ነው። ይሁን እንጅ በአቢይ ሀረጉ ውስጥ ሊገኝ የሚችል ሌላም የአጎላማሽ አይነት አለ። የእሱን አገባብ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

(ሀ) ካሳ [በርግጥ [በመኪና ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል]] 8
(ለ) ካሳ [በፍፁም [በመኪና ወደ ትምህርት ቤት አይሄድም[]

በምሳሌ (ሀ) በርግጥ የሚለው ተውሳከ ግሳዊ አጎላማሽ ነው። ተግባሩ፣ በመኪና ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል በሚለው አቢይ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀውን ተግባር ርግጠኝነት መግለፅ ነው። በምሳሌ (ለ)፣ በፍፁም የሚለው እንደዚሁ ተውሳከ

[6] እንዴ የሚለው የመስተዓምራዊ ሀረግ መሪ፣ አንድ ጊዜ የሚለው ስማዊ ሀረግ ጉራጅ ነው። በዚህ ቅርፁ መስተዓምራዊ ነው። ሌሎቹም በዚሁ አይነት ሁለቴ፣ ሶስቴ፣ ወዘተ፣ እያሉ መጣኝ የሚሆኑበት ስርዓት አለ። በርዓቱ ሀረጎችን ወደ ተራ ቃልነት የሚለውጥ ነው፡

ግሳዊ አንሳማሽ ሲሆን፣ በእቢዩ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀው ተግባር ሀሰት መሆኑን ይገልፃል። እንደነዚህ ያሉ አንሳማሾች ቀደም ሲል ካየናቸው፣ እንደ <u>በመኪና</u> ካሉት አንሳማሾች የተለዩ ናቸው። እንደ <u>በመኪና</u> ያሉት በንዑስ ሀረጉ የሚገለፀውን ድርጊት የአፈፃፀም ሁኔታ የሚያሳዩ ሲሆኑ፣ እነዚህኞቹ ግን የድርጊቱን ሀሰትነት ወይም ርግጠኝነት የሚያስታውቁ ናቸው። ይህ ደግሞ የቋዋንቋዋው ተናጋሪዎች ስለ ድርጊቱ ያላቸውን አመለካከት የሚገልፅ እንጅ፣ የድርጊቱን ያፈፃፀም ሁኔታ የሚያሳይ አይደለም። የድርጊቱ የአፈፃፀም ሁኔታና በድርጊቱ የሚገለፀው ሀሳብ ውነትነት ወይም ሀሰትነት የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው።

እንደ <u>በርግጥ</u> ያሉ አንሳማሾች ከሌሎቹ አንሳማሾች በግብር ብቻ ሳይሆን፣ በአገባብም የተለዩ ናቸው። እንደ <u>በመኪና</u> ያሉት በእቢዩ ግሳዊ ሀረግ ውስጥ ብቻ ሲገቡ፣ እንደ <u>በርግጥ</u> ያሉት ግን ከእቢዩ ሀረግ አልፈው ከአረፍተ ነገሩ ጋርም ሲዋቀሩ ይችላሉ። ሲዋቀሩም በአረፍተ ነገሩ መነሻ ወይም መድረሻ ላይ በመግባት ነው። የሚከተለውን ለአብነት እንመልከት።


[በርግጥ [ካሳ ትናንት ወደ ጎንደር ሄዶአል]] 9

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ <u>በርግጥ</u> የሚለው ገላጭ የተዋቀረው [ካሳ ትናንት ወደ ጎንደር ሄዶአል] ከሚለው አረፍተ ነገር ጋር ነው። ተግባሩም አረፍተ ነገሩ ያዘለውን ሀሳብ ውነትነት መግለፅ ነው። በዚህ አወቃቀር መሰረት ገላጭነቱ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ለእቢዩ ግሳዊ ሀረግ ሳይሆን፣ ለሙሉው አረፍተ ነገር ነው። ስለዚህም አረፍተ ነገራዊ አንሳማሽ ሲባል ይችላል። ከዚህ ላይ ታዲያ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም እንደ <u>በርግጥ</u> ያሉ አንሳማሾች መሰረታዊ መዋቅራዊ ቦታ በተራ ቁጥር (8) እንደሚታየው፣ ከእቢዩ ግሳዊ ሀረግ ጋር ነው? ወይስ በተራ ቁጥር (9) እንደሚታየው፣ ከአረፍተ ነገሩ ጋር? ተግባራቸው የአረፍተ ነገሩን ሀሳብ መግለፅ ከሆነ፣ መሰረታዊ ቦታቸውም በተራ ቁጥር (9) እንደሚታየው፣ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ መሆን አለበት። ይሁን እንጅ፣ የነገሩ ርግጠኝነት ወይም ሀሰትነት በእቢዩ ግሳዊ ሀረግ ይዘት ላይ ከሆነ፣ መዋቅራዊ ቦታቸው በተራ ቁጥር (8) እንደሚታየው፣ በዚሁ ሀረግ መነሻ ላይ ይሆናል። ርግጠኝነቱ በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀው ሀሳብ ከሆነ፣ የአንሳማሹ መዋቅራዊ ግንኙነት ከዚሁ ሀረግ ጋር ይሆናል። ስለዚህም እንደ <u>በርግጥ</u> ያሉ አንሳማሾች መዋቅራዊ ቦታ የረጋ ሳይሆን ተለዋዋጭ ነው። እንዴት እንደሚለዋወጥ ከሚከተሉት ምሳሌዎች መገንዘብ ይቻላል።


(ሀ) [ካሳ [በርግጥ [ትናንት ወደ ጎንደር ሄዶአል]]] 10
(ለ) [ካሳ[ትናንት [በርግጥ [ወደ ጎንደር ሄዶአል]]]]

በምሳሌ (ሀ)፣ <u>በርግጥ</u> የሚለው ሀረግ የተዋቀረው ከእሱ ቀጥሉ ከሚገኘው [ትናንት ወደ ጎንደር ሄዶአል] ከሚለው አቢይ ግሳዊ ሀረግ ጋር ነው። ርግጡም ይህ ሀረግ ያዘለው ሀሳብ ነው። በምሳሌ (ለ) ደግሞ፣ ይኸው <u>በርግጥ</u> የሚለው ሀረግ የተዋቀረው [ወደ ጎንደር ሄዶአል] ከሚለው ንዑስ ሀረግ ጋር ነው። ርግጡም ይህ ንዑስ ሀረግ የሚገልፀው ሀሳብ ነው። የአወቃቀሩን ሁኔታ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ግሳዊ ሀረጎቹን ብቻ በዕፀ-መዋቀር እንደሚከተለው እናሳያለን።

(ሀ) 11




(ለ)




በ11(ሀ) ውስጥ፡ በርግጥ የሚሰው ሀረግ በዋናው አቢይ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ) ስር ተዋቅሮአል። ገላጭነቱም ለአቢዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ነው። በ11(ለ) ውስጥ ግን ይኸው ሀረግ በአቢዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ስር ተዋቅሮ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1)ን ይገልፃል። ይህን ሊያደርግ የቻለውም ከዋናው አቢይ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ) ወርዶ ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ጋር በመዳበል ነው። በ11(ለ) ውስጥ፥ ከዋናው አቢይ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ) ስር የሚታየው ነጠብጣብ፡ ሀረጉ ከመውረዱ በፊት የነበረበትን መሰረታዊ ቦታ ያመለክታል።

አረፍተ ነገራዊ ገላጮች ከመሰረታዊ ቦታቸው እየተነሱ ወደ ሌላ ቦታ የመንቀሳቀስ ዕድላቸው ከሌሎች ገላጭ ሀረጎች የበለጠ ነው። ሌሎች ገላጮች የሚንቀሳቀሱት በአብዛኛው ወደ አረፍተ ነገሩ መነሻ ነው። አረፍተ ነገራዊ ገላጮች

ግን በተራ ቁጥር (9) ከሚታየው መሰረታዊ ቦታቸው እየተነሱ ወደ አረፍተ ነገሩ መሀል በመግባት፣ ከአቢዩም ሆነ ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ጋር የመዳበል፣ እንዲሁም ወደ አረፍተ ነገሩ መድረሻ የመዝለቅ ዕድል አላቸው። ለንፅፅር ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) [ካሳ [በድንገት [ወደ ጎንደር ሄደ]]] 12
(ለ) [በድንገት[ካሳ [— [ወደ ጎንደር ሄደ]]]]

(ሀ) [ምናልባት [ካሳ በድንገት ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል]] 13
(ለ) [ካሳ ምናልባት [በድንገት ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል]]
(መ) [ካሳ በድንገት ምናልባት [ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል]]
(ሰ) [ካሳ በድንገት ወደ ጎንደር ምናልባት [ሄዶ ይሆናል]]
(ረ) [[ካሳ በድንገት ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል]፣ ምናልባት]

በምሳሌ 13(ሀ)፣ ምናልባት የሚለው አገላማሽ [ካሳ በድንገት ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል] ከሚለው አረፍተ ነገር ጋር ተዋቅሮአል። ተግባሩም አረፍተ ነገሩ ያዘለውን ሀሳብ አጠራጣሪነት መግለፅ ነው። በምሳሌ፣ (ለ) [በድንገት ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል] የሚለውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ፣ በምሳሌ (መ) [ወደ ጎንደር ሄዶ ይሆናል] የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ፣ በምሳሌ (ሰ) [ሄዶ ይሆናል] የሚለውን መሪ ግስ ይገልፃል። በመጨረሻም፣ በምሳሌ (ረ) እንደገና ሙሉውን አረፍተ ነገር ይገልፃል። ይህ የግሎቹ እንቅስቃሴ በምሳሌ 12(ለ) በድንገት የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ካደረገው እንቅስቃሴ እጅግ የሰፋ ነው። ይህም አረፍተ ነገራዊ ግሎች ከግሳዊ ሀረግ ግሎች የሚለዩበት ዋና ባህሪ ነው። እንደ ልብ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ይንሸራሸራሉ። ይህ ሁኔታ ቃለ አጋኖዎችን ሊያስታውሰን ይገባል፡፡ እነሱም እንደዚሁ የትሜ ናቸውና፡፡

ሌላው በሁለቱ ግሎች መካከል ያለው ልዩነት ወደ ስማዊ ሀረግነት ሲለወጡ የአዛማጅ አረፍተ ነገር መሪ ከመሆን ጋር የተያያዘ ነው። የግሳዊ ሀረግ አገላማሾች የአዛማጅ አረፍተ ነገር መሪ ለመሆን ሲችሉ፥ አረፍተ ነገራዊ ግሎች ግን ይህን ማድረግ አይችሉም። ይህን ልዩነት ከሚከተሉት ምሳሌዎች ንፅፅር መገንዘብ ይቻላል።

(ሀ) ካሳ በመኪና ወደ ትምህርት ይሄዳል 14
(ለ) ካሳ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄድበት መኪና

(ሀ) ካሳ በርግጥ ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል። 15
(ለ) * ካሳ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄድበት ርግጥ

በምሳሌ 14(ሀ) ውስጥ በመኪና የሚለው የግሳዊ ሀረግ ግሳጭ፣ በምሳሌ 14(ለ) የሚሄድበት መኪና ወደሚል ስማዊ ሀረግ መለወጥ ችሎአል። የሚሄድበት የሚለው

አዛማጅ አረፍተ ነገር ሲሆን፣ መሪው መኪና የሚለው ስም ነው። በምሳሌ 15(ሀ) ውስጥ፣ በርግጥ የሚለው አረፍተ ነገራዊ ገላጭ ግን፣ በ15(ለ) ውስጥ እንደሚታየው ወደ ስማዊ ሀረግነት ሊለወጥ አልቻለም። ይህም በአረፍተ ነገራዊ ገላጮችና በግሳዊ ሀረግ ገላጮች መካከል ላለው ልዩነት ተጨማሪ ማስረጃ ነው። የግሳዊ ሀረግ ገላጮች ብቻ ወደ ስማዊ ሀረግነት የመለወጥ ችሎታ አላቸው።

እንደ ምናልባት ያሉ አረፍተ ነገራዊ ገላጮች፣ እንደ በመኪና ካሉ ከግሳዊ ሀረግ ገላጮች የሚለዩበት ሌላም ሰዋሰዋዊ ባህሪ አለ። ይህም አፅንዖት ነው። የግሳዊ ሀረጎች የተለየ ባህሪ ይመለላል። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) [ካሳ ምናልባት በመኪና ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ ይሆናል] 16
(ለ) በመኪና ነው [ካሳ ምናልባት ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ የሚሆነው]
(መ) ? ምናልባት ነው [ካሳ በመኪና ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ የሚሆነው]

ምሳሌ (ሀ) በለሆሳስ (ያለአፅንዖት) የተነገረ አረፍተ ነገር ነው። ምሳሌ (ለ)፣ በመኪና የሚለው የግሳዊ ሀረግ ገላጭ በአፅንዖት የተነገረበት አረፍተ ነገር ነው። ሀረጉ አፅንዖት ያገኘው፣ ነው ከሚለው ግስ ጋር ተዋቅሮ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ በመገኘቱ ነው። በዚህም ምክንያት ይህ ሀረግ ያዘለው ሀሳብ ከሌሎቹ የበለጠ አፅንዖት ሊያገኝ ችሎአል። በምሳሌ (መ)፣ በተመሳሳይ ሁኔታና ቦታ፣ ምናልባት የሚለው አረፍተ ነገራዊ ገላጭ፣ ነው ከሚለው ግስ ጋር ተዋቅሮ ገብቶአል። ይሁን እንጅ፣ የአረፍተ ነገሩ ተቀባይነት አጠያያቂ ሆኖአል። ከዚህም አረፍተ ነገራዊ ገላጮች አፅንዖታዊ መዋቅር እንደሌላቸው፣ ማለትም በአፅንዖት ሲነገሩ እንደማይችሉ መገንዘብ ይቻላል።

ከዚህ በላይ በዝርዝር ያየናቸው ሁኔታዎች የሚያመለክቱት፣ እንደ ምናልባት ያሉ ሀረጎች እንደ በመኪና ካሉት በአገባብ የተለዩ መሆናቸውን ነው። ልዩነታቸው ያገባብ ብቻ ሳይሆን፣ የተግባርም ነው። እንደ ምናልባት ያሉት ሀረጎች የሚገልፁት፣ አንድ ድርጊት የተፈፀመበትን ሁኔታ ሳይሆን፣ የድርጊቱን ውነትነት ወይም አጠራጣሪነት ነው። ይህ ደግሞ እንደየግለሰቡ ሊለያይ የሚችል የዕምነት ወይም የስሜት ጉዳይ ነው። በዚህም ምክንያት አንዱ ውነት የሚለውን፣ ሌላው ሀሰት ሊለው ይችላል። ስለዚህም እንደዚህ ያሉትን ከግል ስሜት ጋር የሚያያዙ ነገሮችን የሚገልፁ ሀረጎችን ከሌሎች ሀረጎች ለይቶ ማየት ያስፈልጋል። ከፍ ሲል ያየነው ያወቃቀር ልዩነትም ይህን የሚያጠናክር ነው። እንደ ምናልባት ያሉ ሀረጎች መሰረታዊ መዋቅራዊ ዝምድና ከአረፍተ ነገሩ ጋር ሲሆን፣ እንደ በመኪና ያሉት ከግሳዊ ሀረጉ ጋር ነው። ስለዚህም በመካከላቸው የርከን ልዩነት አለ።

በዚህ ንዑስ ክፍል እስካሁን የተመለከትነው የኢሳቢ ግሳዊ ሀረግን ውስጣዊ ያወቃቀር ስርዓት ነው። ኢሳቢ ግሶች መሙሊያ ሀረግ ሊኖራቸው እንደሚችልና ከዚህም ሀረግ ጋር ንዑስ ግሳዊ ሀረጋቸውን እንዴት እንደሚመሰርቱ አይተናል። መሙሊያው ሀረግ ድርጊት ተቀባይ ወይም ተሳቢ ስማዊ ሀረግ እንደማይሆንም ተመልክተናል። ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ከተለያዩ ገላጭ መስተዋድዳዊ ወይም ስማዊ

ሀረጎች ጋር እየተዋቀረ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ እንደሚመሰርት ገልፀናል። አቢይ ሀረጉም በተራው ከመጣኝ መሰተዓምር ጋር ተቀናጅቶ ከፍተኛውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ ሲመሰርት አይተናል። በመጨረሻም እረፍተ ነገራዊ ገላጮች ያልናቸው፣ ያንድን ሀረግ ወይም እረፍተ ነገር ሀሳብ ውነትነት ወይም ሀስትነት የሚገልፁ ሀረጎችን ባሀሪ ከግሳዊ ሀረግ ገላጮች ጋር እያነፃፀርን ተመልክተናል። ከዚህ ቀጥሰን ደግሞ የሳቢ ግሳዊ ሀረጎችን ስርዓት እንመለከታለን።

## *ሳቢ ግሳዊ ሀረግ*

ባለፈው ንዑስ ክፍል መግቢያ አካባቢ እንደተገለፀው፣ ሳቢ ግሶች የሚባሉት የድርጊት ግሶች ናቸው። ድርጊቱ የሚፈፀመው በአድራጊ ነው። የሚፈፀመውም በተደራጊ ላይ ነው። አድራጊና ተደራጊ በሰማዊ ሀረግ መልክ ይከሰታሉ። ተደራጊው ሰማዊ ሀረግ ተሳቢ ይባላል። ተሳቢነቱም ለሳቢው ግስ ነው። ሳቢና ተሳቢ እንድ ላይ ተዋቅረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግን ይመሰርታሉ። የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው።

(ሀ) ካሳ [ልጁን ገረፈው] 1
(ለ) እስቴር [እንቁላሉን ሰበረችው]

በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ፣ በየቅንፉ ውስጥ የሚታዩት መዋቅሮች ንዑስ ግሳዊ ሀረጎች ናቸው። የመዋቅሮቹ መሪዎች ግሶቹ ናቸው። ሳቢ ስለሆኑም መሙሊያዎቻቸው ተሳቢ ስማዊ ሀረጎች ናቸው። ተሳቢ ናቸው የምንልበት ምክንያት፣ ለተሳቢነት ምልክት ናቸው የሚባሉትን መስፈርቶች ስለሚያሙዋሉ ነው። መስፈርቶቹም የሚከተሉት ናቸው።

(ሀ) ስማዊ ሀረጉ ከሳቢ ግስ ጋር የሚዋቀር ከሆነ፣
(ለ) ከሳቢ ግስ ጋር ሲዋቀር፣ በግሱ አምድ ላይ የራሱን አፀፋ ካስከተለ፣
(መ) /-ን/ የሚለውን ምዕላድ በመድረሻው ላይ ካሳየ፣
(ሠ) ግሱ ተደራጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ ተሳቢው ስማዊ ሀረግ የዚሁ ግስ ባለቤት ሆኖ መግባት ከቻለ፣
(ረ) በግሱ ለተገለፀው ድርጊት ተደራጊ ወይም ተጠቂ ከሆነ።

ከነዚህ መስፈርቶች አንፃር በ1(ሀ) ውስጥ የሚታየውን፣ ልጁን የሚለውን ስማዊ ሀረግ እንመርምረው። ሀረጉ ገረፈው ከሚለው ሳቢ ግስ ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። በግሱ መድረሻ ላይ /-ኡ/ የሚል ቅጣይ ምዕላድ አለ። ይህ ምዕላድ ልጁ የሚለው ስማዊ ሀረግ አፀፋ ነው። የሚያመለክተው የዚህን ተሳቢ ሀረግ መሪ መደብ፣ ቁጥርና ፆታ ነው። በስሙ መድረሻ ላይ /-ን/ የሚል ቅጣይ ምዕላድ ይታያል። ይህም ስማዊ ሀረጉ ተሳቢ ስመሆኑ ምልክት ነው። ግሱ ተደራጊ ሲሆን፣ ቅርፁ ተገረፈ

የሚል ይሆናል። <u>ልጁ</u> የሚለው ተሳቢ ሀረግም የዚህ ግስ ባለቤት ሆኖ እንደሚከተለው ሊገባ ይችላል።

ልጁ ተገረፈ 2

በመጨረሻም፣ በምሳሌ 1(ሀ)ም ሆነ በምሳሌ (2) ልጁ የሚለው ስማዊ ሀረግ ግሱ የሚገልፀው ድርጊት ተጠቂ ነው። ርግጥ፣ ይህ መስፈርት ትርጉማዊ ነው። ስለሆነም አገይ ሌሎቹ መስፈርቶች በቅርፅ ወይም በአገባብ ሲረጋገጥ አይችልም።

በዚህ አይነት ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሙዋላ ስማዊ ሀረግ ሁሉ ተሳቢ ሲባል፣ ከአገይዚህ ያለ ስም ጋር የሚዋቀር ግስም ሳቢ ይባላል። ሳቢና ተሳቢ አንድ አካል በመሆን ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ። ግሱ የሀረጉ መሪ ሲሆን፣ ስማዊ ሀረጉ (ተሳቢው) መሙሊያው ነው። ስለ መሙሊያ ቀደም ሲል ስለ ስማዊ ሀረግ ስንወያይ የጠቀስነውን እናስታውስ። መሪው ግስ ሙሉ ሀሳብ እንዲሰጥ የሚያደርጉ ሀረጎች ናቸው።

ከፍ ሲል ተሳቢ ስማዊ ሀረግ /-ን/ የምትለዋን ምዕላድ ሊያስከትል እንደሚችል ገልፀናል። ይህች ምዕላድ ግን ሁል ጊዜ ተሳቢን ላታመለክት ትችላለች። የሚከተለውን እንመልከት።

ካሳ አገሩን ሄደ 3

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ <u>አገሩን</u> የሚለው ሀረግ <u>ሄደ</u> ከሚለው ግስ ጋር ተዋቅሮ <u>አገሩን ሄደ</u> የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። /-ን/ የምትለዋ ምዕላድም <u>አገሩ</u> ከሚለው ስማዊ ሀረግ መድረሻ ላይ ተቀጥላለች። ይሁን እንጅ፣ አገሩ የሚለው ስማዊ ሀረግ ተሳቢ አይደለም። ምክንያቱም ግሱ ሳቢ አይደለም። ስማዊ ሀረጉ ተሳቢ ካልሆነ፣ ምዕላድዋን ለምን አስከተለ?

ርግጥ ነው፣ ግሱ ሳቢ አይደለም። የሚያመለከተውም አንድ ሰው አንድን ድርጊት በሌላ አካል ላይ ሲፈፅም ሳይሆን፣ ራሱ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ነው። ስለዚህም እንደ <u>ሄደ</u> ያሉ ግሶች የእንቅስቃሴ ግሶች ይባላሉ። የእንቅስቃሴውን መድረሻ ቦታ የሚገልፅ ሀረግ በመሙሊያነት ይፈልጋሉ። የዚህ አይነት ተግባር ያለው ሀረግ ደግሞ ስማዊ ሳይሆን የመድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። መስተዋድዱም /-ን/ ነው። በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ ያለው ተግባር <u>ወደ</u> ከሚለው መስተዋድድ ተግባር ጋር አንድ ነው። ስለዚህም <u>አገሩን ሄደ</u> በማለት ፋንታ፣ <u>ወደ አገሩ ሄደ</u> ማለት ይቻላል። ከዚህ ሁኔታ ሁለት /-ን/ዎች እንዳሉ እንረዳለን። አንዱ ተሳቢነትን የሚያመለክት ምዕላድ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ መድረሻን የሚያመለክት

መስተዋድድ ነው[9]። ሁኔታው ሞክሼ ምዕላዶች በቋዋንቋዋው ውስጥ በብዛት እንዳሉ ቀደም ሲል የገለፅነውን ሊያስታውሰን ይችላል። ወደ ሳቢ ግሶች እንመለስ።

ሳቢ ግሶች በሁለት ይከፈላሉ። አከፋፈላቸውም በሚፈልጉት የተሳቢ ብዛትና አይነት ላይ የተመሰረተ ነው። በአንድ በኩል፣ አንድ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ብቻ የሚፈልጉ አሉ። እነዚህም ከፍ ሲል ያየናቸው እንደ ገረፈ እና ሰደበ ያሉት ሲሆኑ፣ ሁለት ተሳቢ የሚፈልጉት ደግሞ እንደ ሰጠ እና ነገረ ያሉት ናቸው። ለእነዚህ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ለተማሪዋ ገንዘብ ሰጣት 4

(ለ) ካሳ ለተማሪዋ ወሬ ነገራት

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ፣ የተሰመረባቸው ሀረጎች ተሳቢዎች ናቸው። በቀጥታ ከግሱ በስተግራ የሚገኙት (ገንዘብና ወሬ) ስማዊ ሀረጎች ሲሆኑ፣ ከእነሱ በስተግራ የሚገኘውና ለተማሪዋ የሚለው ሀረግ ስማዊ ሳይሆን፣ መስተዋድዳዊ ነው። በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ሁለቱ ሀረጎች ርቱዕና ኢርቱዕ ተሳቢዎች በመባል ይታወቃሉ። ትርጉማቸውም እንደ ቅደም-ተከተላቸው ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ማለት ነው። ርቱዕ የሚባለው ስማዊ ሀረጉ ሲሆን፣ ኢርቱዑ ደግሞ መስተዋድዳዊው ሀረግ ነው። ኢርቱዕ የተባለበት ምክንያት ስማዊ ሀረጉ ከግሱ ጋር ያለው መዋቅራዊ ግንኙነት በቀጥታ ሳይሆን፣ በመስተዋድዳዊው ሀረግ በኩል በመሆኑ ነው።

እንደነዚህ ያሉ ምሳሌዎች የተሟላ ሀሳብ ሊሰጡ የሚችሉት ሁለቱም ተሳቢዎች በቦታቸው ሲገኙና ከግሱ ጋር ሲዋቀሩ ብቻ ነው። ለምሳሌ ከላይ በተራ ቁጥር 4(ሀ) የሚታየውን አረፍተ ነገር እንደሚከተለው እናስቀምጠው።

?ካሳ ለተማሪዋ — ሰጣት 5

የዚህ አረፍተ ነገር ተቀባይነት አጠራጣሪ ነው ፣ ምክንያቱ ከሁለት ተሳቢዎች አንዱ በቦታው አለመገኘቱ ነው። በቦታው ያልተገኘው ሀረግ ርቱዕው ተሳቢ ነው። ባለመገኘቱም አረፍተ ነገሩ የተሟላ ሀሳብ ሊሰጥ አልቻለም። እንደዚህ ያለ አረፍተ ነገር በንግግር መካከል ሲመጣ፣ የጎደለውን ሀሳብ ከአጠቃላዩ የነገር አካሄድ ማወቅ ስለሚቻል፣ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል። የንግግር መጀመሪያ ሲሆን ወይም ብቻውን ሊነገር ግን ፈፅሞ አይችልም።

---

[9] /-ን/ መድረሻን ብቻ ሳይሆን ሌሎች መስተዋድዶችንም ወክላ ልትገባ ትችላለች። ለምሳሌ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

አስቴር ብዕሩን ደብዳቤ ፃፈችበት

በዚህ ምሳሌ /-ን/ ማድረጊያ መስተዋድድ ነች። ለዚህ ማስረጃው ይህኑ አረፍተ ነገር፥

አስቴር በብዕሩ ደብዳቤ ፃፈችበት

ማለት፣ የሚቻል መሆኑ ነው። ሁኔታው /-ን/ ተውላጠ መስተዋድድ ነች የሚያሰኝ ነው።

የሁለቱ ተሳቢ ሀረጎች መሰረታዊ አገባብ በተራ ቁጥር (4) እንደሚታየው ነው። ይሁን እንጅ ይህ አገባብ ሊፋለስ ይችላል። ይህ ሲሆን፣ ምሳሌ 4(ሀ) የሚከተለውን ይመስላል።

ካሳ ገንዘብ ለተማሪዋ ሰጣት 6

በዚህ ምሳሌ ውስጥ ርቱዑ ተሳቢ ከኢርቱዑ ተሳቢ ቀድሞ ገብቶአል። ይህ በመሆኑ ግን የትርጉም ለውጥ አልተከሰተም። ተሳቢዎቹ ያለትርጉም ለውጥ ቦታ መለዋወጣቸው በአንድ ርከን ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ሊያሳይ ይችላል። ይህን ቀደም ሲል ስለ አጎላማሽ ሀረጎች በንወያይ ተመልክተነዋል።

ተሳቢ ሀረጎች ከአጎላማሽ ሀረጎች የሚለዩት በሁለት ሁኔታዎች ነው። እነዚህም (1) በቀጥታ ከግስ ጋር የሚዋቀሩ መሙሊያ፣ ብሎም ተሳቢ መሆናቸውና (2) ወደ ስማዊ ሀረግነት ሲለወጡ በአዛማጁ ግስ ላይ መስተዋድዳዊ አፀፋ አለማሳየታቸው ነው። መስተዋድዳዊ አፀፋ ማሳየት የአጎላማሾች አይነተኛ ባህሪ ነው። ከዚህ አንፃር በተራ ቁጥር (8) የተሰጠው አረፍተ ነገር ወደ ስማዊ ሀረግ ሲለወጥ የሚከተለውን ይመስላል።


ካሳ ገንዘብ የሰጣት ተማሪ 7

በተራ ቁጥር (6) ውስጥ፣ <u>ለተማሪዋ</u> የነበረው መስተዋድዳዊ ሀረግ በ(7) ውስጥ የአዛማጁ ሀረግ መሪ በመሆን ወደ ተ<u>ማሪ</u> ተለውጦአል። በአዛማጁ ግስ ውስጥም ምንም የመስተዋድድ አፀፋ የለም። <u>ለተማሪዋ</u> የሚለው ሀረግ አጎላማሽ ቢሆን ኖሮ፣ በአዛማጁ ግስ ውስጥ የመስተዋድድ አፀፋ ይታይ ነበር። ይህም እንደሚከተለው ሲሆን ነው።

(ሀ) ካሳ <u>ከተማሪዋ ላይ</u> ገንዘብ ወሰደ 8
(ለ) ካሳ ገንዘብ የወሰደ<u>ባት</u> ተማሪ

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ <u>ከተማሪዋ ላይ</u> የሚለው አጎላማሽ መስተዋድዳዊ ሀረግ፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ በሚታየው የአዛማጅ ግስ ላይ /-ብአት/ በሚል አፀፋ ተመልክቶአል። ይህም፣ በአዛማጅ አረፍተ ነገር ግስ ላይ በመስተዋድድ አፀፋ መጠቀስ፣ የአጎላማሽ ሀረግ ባህሪ ነው ያልነውን ያረጋግጣል።

ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ርቱዕና ኢርቱዕ ተሳቢዎች ከመሪ ግስ ጋር ተዋቅረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ። አመሰራረቱን በሚከተለው ዕፀ-መዋቀር እናሳያለን።




8

ይህ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ነው፡፡ የሚገልፀውም ገንዘብ ለተማሪዋ የመስጠትን ድርጊት ብቻ ነው። የሰጭውን ማንነት፣ የአሰጣጡን ሁኔታ፣ ጊዜ፣ ቦታ፣ ምክንያት፣ ወዘተ፣ አይገልፅም። እንደዚሀ ያሉትን ተጨማሪ መረጃዎች መስጠት ሲያስፈልግ፣ ልዩ ልዩ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን ወይም ወደፊት እንደምናየው ጥገኛ አረፍተ ነገሮችን ከንዑሱ ሀረግ በፊት እንደሚከተለው ማስገባት ያስፈልጋል።


[በፖስታ [ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጣት]] 10

<u>በፖስታ</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፣ [ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጣት[ የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ቀድሞ ገብቶአል። ይህ መሰረታዊው ቦታው ነው። በዚሀ ቦታ ሆኖ ገንዘቡ የተሰጠበትን ዘዴ ወይም መንገድ ይገልፃል።

እንዳንድ ጊዜ ተሳቢዎቹ ሀረጎች እየቀደሙት ሊገቡ ይችላሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ የሀረጎቹ ቅደም- ተከተል እንደሚከተለው ይሆናል።

(ሀ) ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ [በፖስታ[– – ሰጣት]] 11
(ለ) ብዙ ገንዘብ ለተማሪዋ [በፖስታ[– – ሰጣት]]

በገልፅ እንደሚታየው፣ ተሳቢዎቹ ሀረጎች በነጠብጣብ የተመለከተውን መሰረታዊ ቦታቸውን ለቀው፣ <u>በፖስታ</u> የሚለውን ገላጭ ሀረግ በመቅደም፣ ከሀረጉ ውጭ ሆነዋል። ይህ አገባብ በአጠቃቀም ጊዜ ለሀረጎቹ አፅንዖት ለመስጠት ሲፈለግ የሚታይ ነው። በተራ ቁጥር (10) የሚታየውን የሀረጎቹን መሰረታዊ አወቃቀር በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።




12


ይህ መሰረታዊው የመሙሊያዎቹ (የተሳቢዎቹ) እና የአንላማዎቹ ሀረግ አቀማመጥ ነው[10]። መሙሊያዎቹ ይህን መሰረታዊ ቦታቸውን እየለቀቁ በተራ ቁጥር (11) እንደሚታየው፣ ከሀረጉ ውጭ ሊሆኑ ይችላሉ። በመሰረታዊው አወቃቀር ደረጃ፣ ይህ አቢይ ሀረግ መጣኝ መስተዋምር ያስፈልገዋል። መስተዋምሩ የሚዋቀረው ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ጋር ነው። ይህ ሲሆን፣ በተራ ቁጥር (10) የሚታየው ሀረግ የሚከተለውን ይመስላል።

[ሁለት ጊዜ [በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጣት]] 13

ይህ ያወቃቀር ስርዓት ባለፈው ንዑስ ክፍል ካየነው ከኢሳቢ ግሶች ያወቃቀር ስርዓት ጋር ተመሳሳይ ነው። ልዩነት ቢኖር፣ መሙሊያ በመያዝና ባለመያዝ፣ እንዲሁም በመሙሊያው አይነትና ተግባር ላይ ነው። ሳቢ ግሶች መሙሊያ ሀረግ የግድ ያስፈልጋቸዋል፤ መሙሊያ ሀረጉም ስማዊና መስተዋድዳዊ ሲሆን፣ ተግባሩ ተሳቢነት ነው። በተራ ቁጥር (13) የተመለከተው አቢይ ሀረግ በስነ-መዋቅር ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል።

[10] መሰረታዊው አገባብ ርባው ተሳቢ ቀድሞ፣ ኢርባው እሱን ተከትሎ የሚገኝበት ነው፤ ለማለት ይቻላል። ተዋረዳዊ አቀማመጣቸውም ከዕፀ መዋቅር (9) እንደሚታየው ሶስትዮሽ ሳይሆን ሁለትዮሽ ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል። ይህም ከትውረት አንፃር ነው። ለጊዜው ወደ ዝርዝሩ አንገባም።

14





ይህ የተሙዋላ ሀሳብ ያዘለ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ነው። ከዚህ ላይ ሊጨመር የሚችለው ገንዘብ የመስጠቱን ተግባር የሚፈፅመውን ሰው የሚጠቁም ስማዊ ሀረግ ነው። ይህ ሀረግ ከዚህ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ጋር ሲዋቀር የምናገኘው እንደሚከተለው ያለ አረፍተ ነገርን ነው።

[ያ ልጅ [ሁለት ጊዜ በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]] 15

በውስጠኛው ቅንፍ ውስጥ የሚታየው፣ አቢዩ ግሳዊ ሀረግ ነው። በውጪኛው ቅንፍ ውስጥ የሚታየው የድርጊቱን ፈፃሚ የሚያመለክተው ስማዊ ሀረግ ነው። ይህ ሀረግ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። አረፍተ ነገሩ የተሙዋላ ሀሳብ ይሰጣል። ይህን ሀሳብ የሚያጠራጥር ወይም የሚያረጋግጥ ሀረግ መጨመር ይቻላል። ሀረጉም የሚዋቀረው ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ከአጠቃለዩ አረፍተ ነገር ጋር ነው። ይህም ሲሆን፣ ከላይ የሚታየው አረፍተ ነገር የሚከተለውን ይመስላል።

[በርግጥ [ያ ልጅ ሁለት ጊዜ በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]] 16

<u>በርግጥ</u> የሚለው አረጋጋጭ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። የሚገኘው ከአረፍተ ነገሩ ውጭ ነው። ከዚህ ቦታ ላይ ሆኖ፣ ሙሉ አረፍተ ነገሩን ያጎላምሳል። ስለዚህም ነው ቀደም ሲል፣ አረፍተ ነገራዊ አጎላማሽ ነው ያልነው። ከአረፍተ ነገሩ ጋር ያለውን መዋቅራዊ ዝምድና እንደሚከተለው እናሳያለን።



17

አረፍተ ነገራዊ አጎላማሾች ከግሳዊ ሀረግ አጎላማሾች የሚለዩባቸው ሁለት ባህሪያት እንዳሉዋቸው ቀደም ሲል ገልፀናል። እነዚህም ወደ ስማዊ ሀረግ ሊለወጡ አለመቻላቸውና በአረፍተ ነገሩ ውስጥ እንደ ልብ ሲንቀሳቀሱ መቻላቸው ናቸው። ይህ ሁኔታ በሚከተሉት ምሳሌዎችም ይታያል፡

(ሀ) ያ ልጅ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ <u>የሰጠበት ፖስታ</u> 18

(ለ) *ያ ልጅ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ <u>የሰጠበት ርግጥ</u>

<u>በፖስታ</u> የሚለው የግሳዊ ሀረግ አጎላማሽ ገንዘብ <u>የሰጠበት ፖስታ</u> ወደሚል ስማዊ ሀረግ መለወጥ ሲችል፣ <u>በርግጥ</u> የሚለው አረፍተ ነገራዊ አጎላማሽ ግን ይህን ማድረግ እንዳልቻለ፣ የምሳሌ (ለ) ተቀባይነት ማጣት ምልክት ነው።

የአረፍተ ነገራዊ አጎላማሾችን የእንደልብ እንቅስቃሴ ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ያ ልጅ <u>በርግጥ</u> [በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል] 19

(ለ) ያ ልጅ በፖስታ <u>በርግጥ</u> [ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]

(መ) ያ ልጅ በፖስታ ለተማሪዋ <u>በርግጥ</u> [ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]

(ለ) ያ ልጅ በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ <u>በርግጥ</u> [ሰጥቶአታል]

(ረ) [ያ ልጅ በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]፣ <u>በርግጥ</u>

<u>በርግጥ</u> የሚለው ሀረግ በተራ ቁጥር (16) ከሚታይበት መሰረታዊ ቦታው በመነሳት፣ ሁሉንም ሀረግ እያቋዋረጠ እስከ አረፍተ ነገሩ መጨረሻ ድረስ እንደሄደ ማየት ይቻላል። በተራ ቁጥር (16) ሙሉውን አረፍተ ነገር ያጎላምሳል። በተራ ቁጥር (19) ግን ከሚገኝበት ቦታ ቀጥሉ ያለውን ሀረግ ብቻ ያጎላምሳል። በ19(ረ) ውስጥ፣ በአረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ ቢገኝም፣ የሚያጎላምሰው ሙሉውን አረፍተ ነገር ነው። ርግጥ፣ አጎለማመሱ በአረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ላይ ሆኖ እንደሚፈፅመው አይደለም፤ ጥንካሬ ይጎለዋል። ማንኛውም በመጨረሻ የሚነገር፣ አንድም መጀመሪያ ተረስቶ ድንገት ትውስ ያለ፣ አለያም አፅንዖት ሊሰጠው ያልተፈለገ ነገር ነው።

ወደ መግቢያው አካባቢ፣ ግሶችን የድርጊትና የሁነት ብለን በሁለት ከፍለን ነበር። እስካሁን ያየነው የድርጊት ግሶችን መዋቅራዊ ባህሪ ብቻ ነው። እነሱንም ኢሳቢና ሳቢ ብለን በሁለት ንዑስ ክፍሎች በመለየት ከንዑስ እስከ አቢይ ሀረግ ድረስ ያለውን ያወቃቀር ስርዓታቸውን ተመልክተናል። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የሁነት ግሶችን ባህሪ እንመረምራለን።

## *የመሆን ግስ ሀረግ*

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የመሆን ግስ የሚባሉት ድርጊትን ሳይሆን፣ ሁነትን ወይም በአንድ ቦታ መገኘትን ያመለክታሉ። ባለቤታቸው ሁዋኝ ወይም ነዋሪ ስማዊ ሀረግ ነው። ሁነትን የሚያመለክቱት ባለቤቱን ለማዊ ሀረግ በአቻነት የሚገልፅ መሙሊያ ይፈልጋሉ። ኑረትን (መኖርን) የሚያመለክቱት ነዋሪው ባለቤት የሚገኝበትን ቦታ የሚያመለክት መሉተዋድዳዊ ሀረግ ይፈልጋሉ። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ አስተማሪ ሆነ (1)
(ለ) ካሳ ጎበዝ ሆነ
(መ) ካሳ አስተማሪ ነው
(ሰ) ካሳ ጎበዝ ነው
(ረ) ካሳ አስተማሪ ይመስላል
(ሽ) ካሳ ጎበዝ ይመስላል
(ቀ) ካሳ ቤት ውስጥ አለ

<u>ሆነ</u>፣ <u>ይመስላል</u> እና <u>ነው</u> አንድ ነገር መሆንን ስለሚያመለክቱ፣ የመሆን ግስ ናቸው። <u>አለ</u> የሚለው በአንድ ቦታ መገኘትን ስለሚያመለክት፣ የመኖር ግስ ነው። መኖርና መሆን ተቀራራቢ ናቸው። ለምሳሌ፣ አንድን ሰው " ናእዚ ሀ ሁን " ስንል፣ እዚህ ቦታ ተቀመጥ ወይም ተገኝ ማለታችን ነው። እዚያ ቦታ ሲቀመጥ ወይም ሲገኝ ደግሞ፣ <u>እዚህ አለ</u> እንላለን። በዚህ ምክንያት ሁለቱንም አይነት ግሶች በአንድ ስም የመሆን ግሶች እንላቸዋለን።

መዋቅራዊ ልዩነት ግን አላቸው፤ ይኸውም፣ የመኖር ግሶች ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ለመመስረት መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲፈልጉ፣ የመሆን ግሶች ቅፅላዊ ወይም ስማዊ ሀረግ የሚፈልጉ መሆናቸው ነው። የሀረጎቹ ተግባርም እንደዚሁ ይለያያል። የመሆን

ግስ መሙሊያዎች ሁዋኙን ባለቤት በአቻነት ሲገልፁ፣ የመኖር ግስ መሙሊያዎች መገኛ አድራሻውን ያመለክታሉ።

ከዚህ ላይ የመኖር ግስን በሚመለከት አንድ ተጨማሪ ተግባር ማንሳት ያስፈልጋል። ይኸውም የአንድን ነገር የመኖር ዓላማ የሚመለከት ነው። አንድ ነገር ዝም ብሎ ሊኖር፣ ወይም ስአንድ ሌላ ነገር ጠቃሚ ሆኖ ሊኖር ይችላል። እንደዚሁ ዝም ብሎ የሚኖረውን፣ ለተለየ ጥቅም ወይም አላማ ከሚኖረው መለየት ያስፈልጋል። ለተለየ ጥቅም የሚኖረው፣ ለማን እንደሚኖር የሚያሳይ መዋቅራዊ ስርዓት አለ። ለምሳሌ ያሀል የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) አሸዋ መንገድ ላይ አለ 2


(ለ) አሸዋ መንገድ ላይ አለኝ

የመጀመሪያው ምሳሌ፣ የአሸዋን በመንገድ ላይ መገኘት ብቻ ያመለክታል። ሁለተኛው አሸዋው ባለቤት (ባለንብረት) እንዳለው ያሳያል። "አለኝ" የሚለውም ሰው ባለንብረቱ ነው። ምሳሌ (ለ) ባለንብረቱን ጨምሮ ሲነገር ላዕላይ ቅርፁ የሚከተለውን ይመስላል[11]።

አኔ አሸዋ መንገድ ላይ አለኝ 3

ወደ ግሶቹ ያወቃቀር ስርዓት እንመለስ። የመሆን ግሶች ስማዊ ወይም ቅፅላዊ ሀረግን መሙሊያ አድርገው ንዑስ ግሳዊ ሀረጋቸውን ይመሰርታሉ። ከላይ ከተራ ቁጥር 1(ሀ-ሸ) የተዘረዘሩትን ምሳሌዎች ንዑስ ሀረግ እንደሚከተለው አጠቃለን በአንድ ዕፁ-መዋቅር እናሳያለን።

4




ቀደም ሲል እንዳየናቸው ግሳዊ ሀረጎች ሁሉ፣ ይሀም ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ከተለያዩ አነላማሾች ጋር እየተዋቀረ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታል። ይሀን በሚከተሉት ምሳሌዎች እናሳያለን።

(ሀ) [አምና [ጎበዝ ነበር]] 5

(ለ) [አሁን [ቤት ውስጥ አለ]]

[11] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ባዩ (1997)ን ይመልከቱ።

በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ፣ <u>እምና</u> እና <u>አሁን</u> የሚሉት ጊዜን የሚያመለክቱ ተውሳከ ግሳዊ ሀረጎች ናቸው። በውስጠኛው ቅንፍ ውስጥ ከሚታዩት ንዑስ ግባዊ ሀረጎች ጋር ተዋቅረው አቢዩን ግሳዊ ሀረግ መስርተዋል። ተግባራቸው በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀውን ሁኔት ከጊዜ አንፃር እየገለፁ ንዑሱን ሀረግ ማጎላመስ ነው። ቦታቸውም ከመሙሊያው በፊት፣ ማለትም በስተግራ፣ ነው። መሙሊያውን ተከትለው ቢገቡ፣ የሀረጉ ተቀባይነት ይቀንሳል። የሚከተለውን እንመልከት።


(ሀ) * ጎበዝ [እምና[ — ነበር] [ 6
(ለ) ?ቤት ውስጥ [አሁን [--- አለ] ]

<u>ጎበዝ</u> እና <u>ቤት ውስጥ</u> የሚሉት መሙሊያ ሀረጎች ናቸው፡፡ መሰረታዊ ቦታቸው በነጠብጣብ የተመለከተው ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ከዚህ መሰረታዊ ቦታ ተነስተው አጎላማሾቹን ስሞች በመቅድም በአቢዩ ሀረግ መነሻ ላይ ሊገቡ ችለዋል። ይህም በመሆኑ የሀረጎቹ ተቀባይነት በእጅጉ ቀንሶአል። ሁኔታው መሙሊያ ሀረጎች ከመሪው ግስ መለየት አይችሉም ያልነውን የሚያጠናክር ማስረጃ ነው።

ቀደም ሲል እንዳየናቸው የድርጊት ግሶች ሁሉ፣ አቢይ የመሆን ግሳዊ ሀረጎችም ከመጣኝ መስተዓምር ጋር እንደሚከተለው ሊዋቀሩ ይችላሉ።

[አንድ ጊዜ [ጎጃም ውስጥ [አስተማሪ ነበር] ] ] 7

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ <u>አስተማሪ</u> የሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ነው። <u>ጎጃም ውስጥ</u> የሚለውም ቦታን የሚገልፅ አጎላማሽ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። <u>አንድ ጊዜ</u> የሚለው ደግሞ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፣ በጎጃም ውስጥ አስተማሪ ሆኖ የኖረበትን የጊዜ መጠን ይገልፃል። አጠቃላይ መዋቅሩ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ሲሆን፣ በዕፀ-መዋቅር በወርድና ተዋረድ ተተንትኖ ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል።



8

ይህ አቢይ ሀረግ ሁዋኙን ባለቤት ከሚገልፀው ስማዊ ሀረግ ጋር እየተዋቀረ፡ ሙሉ ሀሳብ የሚሰጥ አረፍተ ነገርን ይመሰርታል። አረፍተ ነገሩም የሀሳቡን ርግጠኝነት ወይም አጠራጣሪነት ከሚገልፁ አረጋጋጭ ወይም አጠራጣሪ አጎላማሾች ጋር እንደሚከተሰው ሊዋቀር ይችላል።

(ሀ) [ያ ሰውየ [አንድ ጊዜ ጎጃም ውስጥ አስተማሪ ነበር]] 9

(ለ) [በርግጥ [ያ ሰውየ [አንድ ጊዜ ጎጃም ውስጥ አስተማሪ ነበር]]]

የመጀመሪያው ምሳሌ [አንድ ጊዜ ጎጃም ውስጥ አስተማሪ ነበር] የሚለው አቢይ ግሳዊ ሀረግ፣ [ያ ሰውየ] ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ አረፍተ ነገር መስርቶአል። ይህ አረፍተ ነገር [በርግጥ] ከሚለው አረጋጋጭ አረፍተ ነገራዊ አጎላማሽ ጋር ተዋቅሮአል። የአጎላማሹ መሰረታዊ ቅንጅት ከአረፍተ ነገሩ ጋር ነው። ይሁን እንጅ፣ ከማንኛውም የአረፍተ ነገሩ ክፍል ጋር ሊዋቀር እንደሚችል ቀደም ሲል በተራ ቁጥር (19) ካየናቸው ምሳሌዎች ተረድተናል። ከማንኛውም ሀረግ ጋር ሲዋቀር፣ የሚፈፀመው ተግባር ተዋቃሪው ሀረግ ያዘለውን ሀሳብ ርግጠኝነት ወይም አጠራጣሪነት መግለፅ ነው። በዚህም የሁነቱን *መቻት* ከሚገልፁት የግሳዊ ሀረግ አጎላማሾች ይለያል።

በዚህ ንዑስ ክፍል በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን። መጀመሪያ፣ ግሶችን የድርጊትና የሁነት ብለን ለየናቸው። የድርጊት ያልናቸው፣ አንድ ሰው ወይም ሀይል በራሱ ወይም በአንድ ሌላ ነገር ላይ የሚፈፅመውን ተግባር የሚገልፁ ናቸው። ግሶች መሙሊያ ሊኖራቸው ወይም ላይኖራቸው ይችላል። እንደ መሙሊያቸው አይነትም ሳቢና ኢሳቢ ተብለው እንደገና በሁለት ይከፈላሉ። ሳቢ የሚባሉት ግሶች መሙሊያ ድርጊት ተቀባዩን ነገር የሚጠቁም ስማዊ ሀረግ ነው። ይህም ሀረግ ተሳቢ ይባላል። ግስና መሙሊያ ተዋቅረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ። መሙሊያው ያለመሪው፣ መሪውም ያለመሙሊያው ብቻውን ሀረግ ሊመሰርት አይችልም። መሪው ያለመሙሊያው ብቻውን ቢቆም፣ ሀሳበ-ጎደሉ ይሆናል። መሙሊየውም ብቻውን ቢገኝ፣ አንድ ነገርን ከመጠቆም አልፎ ግሳዊ ሀረግ ሊሆን አይችልም። ግሳዊ መሪ የግድ ያስፈልገዋል።

ከመሙሊያና ከመሪ የሚዋቀረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ፣ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ገላጭ አጎላማሾች ያስፈልጉታል። እነዚህ በአብዛኛው መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው። ተግባራቸውም በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀውን ድርጊት ከጊዜ፣ ከመሳሪያ፣ ከዓላማ፣ ወዘተ፣ አንፃር መግለፅ ነው። ርስበርስ ያላቸው ቅደም-ተከተላዊ ስርዓትም *ዘፈቀዳዊ* ነው። በዚህም ከመሪው ግስ ጋር ጥብቅ ትስስር ካለው ከመሙሊያው ሀረግ ይለያሉ።

ንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ከአጎላማሾቹ ጋር ተዋቅሮ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታል። ይህም አቢይ ግሳዊ ሀረግ ከመጣኝ መስተዓምሮች ጋር ተዋቅሮ ዋናውን ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታል። ሀረጉ ዋና አቢይ ሀረግ የሚባልበት ምክንያት

ያዘለው ሀሳብ ሙሉ በመሆኑ ነው። የተዋቀሪዎቹ ቅደም-ተከተላዊ ስርዓት እንደሚከተለው ነው።

መስተዓምር- አጎላማሽ - መሙሲያ - መሪ 10

ይህ ቅደም-ተከተላዊ ስርዓት ተዋረዳዊውን ዝምድናም ያንፀባርቃል። ካሁን በፊት በስማዊ ሀረግ ውስጥ እንዳየነው፣ ሀረጉ ቀኝ መሪ ነው። መሪው ግስ ሁሉንም ተዋቀሪዎቹን አስቀድሞ በቀኝ በኩል ይገኛል ማለት ነው።

## ቅፅላዊ ሀረግ

እንደ ስምና እንደ ግስ ሁሉ፣ ቅፅሉችም ከተለያዩ መሙሊያዎች፣ አጎላማሾችና መስተዓምሮች ጋር በየደረጃው እየተዋቀሩ ንዑስና አቢይ ቅፅላዊ ሀረጋቸውን ይመሰርታሉ። በዚህ ንዑስ ክፍል ዝርዝር ሁኔታውን እንመለከታለን። ወደ ዝርዝሩ ከመግባታችን በፊት፣ ስለ ቅፅሉች በክፍል ሁለት የጠቀስነውን እዚህ ላይ እንደገና ማስታወስ እንፈልጋለን። ይኸውም የአማርኛ ቅፅሎች የስም፣ ወይም የግስ ስር ውልዶች መሆናቸው ነው። ይህ ሲባል ግን ነባር ቅፅሉች የሉም ማለት አይደለም። ርግጥ፣ ጥቂት የዚህ አይነት ቅፅሎች አሉ። እነሱም እንደ የዋሀ፣ ብልህ፣ ትሁት፣ ደግ፣ ወዘተ፣ ያሉ ናቸው። እንደነዚህ ያሉ ቅፅሎች ነባር ስማዊ ወይም ግሳዊ እቻ የላቸውም። ለምሳሌ፣ ጥቁር ለሚለው ቅፅል፣ ጠቆረ የሚል ግሳዊ እቻ እንዳለው ሁሉ፣ የዋሀ የሚለው የወኸ የሚል ግሳዊ እቻ የለውም። የግሳዊነት ሀሳብ የሚገለፀው ቀደም ሲል በጠቀስነው በመሆን ግስ አማካኝነት ነው። ይኸውም ካሳ የዋሀ ሆነ በማለት ነው። ግሳዊ እቻ ያላቸው ቅፅሉች፣ ቅፅላዊ ሀሳቡን በሁለቱም ሲገልፁ፣ ግሳዊ እቻ የሌላቸው ግን በአንዱ፣ ይኸውም በቅፅሉ ብቻ ይገልፃሉ። ለአብነት የሚከተሉትን እያነፃፀርን እንመልከት።

(ሀ) ከሳ ጎበዝ ሆነ
(ለ) ካሳ ጎበዘ
(መ) ካሳ ብልህ ሆነ
(ሰ) * ከሳ በለኸ

ግሳዊ እቻ የሌላቸው ቅፅሉች በ1(መ) እንደሚታየው፣ ከመሆን ግስ ጋር በመዋቀር ቅፅላዊ ባህሪን ይገልፃሉ። ሁኔታው ነባር ቅፅሎች በብዛት እንደሌሉ ያሳያል። ይሁን እንጅ፣ ቅፅሎችን ነባርና ውልድ ብለን በሁለት ከመክፈል አያግደንም። ትንሽም ቢሆኑ፣ ነባር የሚባሉ ቅፅሎች አሉና።

ውልድ የሚባሉት ራሳቸው በሁለት ሲከፈሉ ይችላሉ። አከፋፈሉ ከሚወለዱብት የቃል ክፍል አኳዋያ ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ቅፅሉች ከስም ወይም ከግስ ስር ስለሚወለዱ፣ በዚሁ መሰረት ከስም የሚወለዱትን ስማዊ፣ ከግስ

የሚወለዱትን ግሳዊ ቅፅል በማለት ልንለያቸው እንችላለን። ስማዊ የሚባሉት እንደ ሆዳም፣ አመለኛ፣ እልኸኛ፣ ወዘተ፣ ያሉት ሲሆኑ፣ ግሳዊ የሚባሉት ደግሞ እንደ ጎበዝ፣ ጥቁር፣ ቀይ፣ ወዘተ፣ ያሉት ናቸው። የሁለቱንም ክፍሎች መዋቅራዊ ስርዓት ከዚህ ቀጥለን በየተራ እንመለከታለን።

## *ስማዊ ቅፅል*

ስማዊ ቅፅሎች ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ከስም የሚመሰረቱ ቅፅሎች ናቸው። መዋቅራዊ ባህሪያቸው እንደተመሰረቱበት ስም ባህሪ ይለያያል። ስሙ መሙሊያ የሚፈልግ ከሆነ፣ ቅፅሉም እንደዚሁ መሙሊያ ይፈልጋል። ስሙ መሙሊያ የማይፈልግ ከሆነ፣ ቅፅሉም አይፈልግም። ባጭሩ ውልድ ቅፅሎች የናታቸውን መዋቅራዊ ባህሪ ይወርሳሉ። ጉዳዩ የቅፅሎች ብቻ አይደለም፣ ስሞችም የተመሰረቱበትን ግስ መዋቅራዊ ባህሪ ይወርሳሉ። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

(ሀ) ሁለት መፅሀፍ <u>ሸጠ</u> 2

(ለ) የሁለት መፅሀፍ <u>ሸያጭ</u>

ምሳሌ 2(ሀ) ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ነው። መሪው <u>ሸጠ</u> የሚለው ሳቢ ግስ ሲሆን፣ የተዋቀረው <u>ሁለት መፅሀፍ</u> ከሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ጋር ነው። 2(ለ) ስማዊ ሀረግ ነው። መሪው <u>ሸያጭ</u> የሚለው ውልድ ስም ነው። የተወለደው <u>ሸጠ</u> የሚለው ሳቢ ግስ ከተወለደበት ስር ነው። ስለሆነም እሱም እንደ ግሱ ከመሙሊያ ጋር ተዋቅሮአል። የሁለቱ ሀረጎች ልዩነት የአይነት እንጅ ያወቃቀር አይደለም። ስማዊና ግሳዊ ከመሆናቸው በስተቀር መዋቅራዊ ይዘታቸውም ሆነ አያያዛቸው ተመሳሳይ ነው።

በዚሁ አይነት የስማዊ ቅፅሎችን መዋቅራዊ ባህሪ እንመለከታለን። ከላይ እንደተገለፀው፣ ስማዊ ቅፅል የሚባሉት ከስም ላይ የሚመሰረቱ ናቸው። እንደዚህ ያሉ ቅፅሎች መሙሊያ የላቸውም። ስለዚህም ንዑስ ሀረጋቸውን የሚመሰርቱት በመሪው ቅፅል አማካኝነት ብቻ ነው። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

(ሀ) [እልኸኛ] 3

(ለ) [አመለኛ]

የመጀመሪያው <u>እልህ</u>፣ ሁለተኛው አ<u>መል</u> ከሚለው ስም ላይ የተመሰረቱ ቅፅሎች ናቸው። ስሞቹ መሙሊያ እንደማይፈልጉ ሁሉ፣ ቅፅሎቹም እንደዚሁ አይፈልጉም። የመጀመሪያውን ምሳሌ ንዑስ ሀረግ እንደሚከተለው እናሳያለን።

ቅሀ1 4

|

ቅ

|

አልኸኛ

ይህ ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ ከአጎላማሽ ሀረግ ጋር በመቀናጀት አቢይ ቅፅላዊ ሀረጉን እንደሚከተለው ይመሰርታል።

(ሀ) አስቴር [[እንደ አባትዋ ] [አልኸኛ]] ነች 5
(ለ) አስቴር [[እንደ አባትዋ ] [አመለኛ]] ነች

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ [አልኸኛ] የሚለው ቅፅል [እንደ አባትዋ] ከሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ [እንደ አባትዋ አልኸኛ] የሚለውን አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ መስርቶአል። ይህ አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ በተራው ከመጣኝ መስተዓምር ጋር ተዋቅሮ ዋናውን አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ እንደሚከተለው ይመሰርታል።

አስቴር [በጣም [እንደ አባትዋ አልኸኛ] ] ነች 6

ቀደም ሲል እንዳየነው፣ የመስተዓምር ቦታ ሁልጊዜ በሀረግ መነሻ ላይ ነው። [በጣም] የሚለው መጣኝ መስተዓምር ቦታም በመሰረቱ በሀረጉ መነሻ ላይ ነው። ይሁን እንጅ፣ [እንደ አባትዋ ] የሚለው አነፃፃሪ ሀረግ እየቀደመው ሊገባ ይችላል። ይህ ሲሆን፥ የቅፅላዊው ሀረግ ቅደም-ተከተል እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል።

(ሀ) [እንደ አባትዋ ] [በጣም [ — አልኸኛ]] 7
(ለ) [እንደ አባትዋ ] [ሁልጊዜ [ — አመለኛ]]

በግልፅ እንደሚታየው፣ [እንደ አባትዋ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ በነጠብጣብ የተሸፈነውን መሰረታዊ ቦታውን ለቆ፣ [በጣም] እና [ሁልጊዜ] የሚሉትን መጣኝ መስተዓምሮች በመቅደም፣ በሀረጉ መነሻ ላይ ገብቶ ይገኛል። ይህ የቅደም-ተከተል ለውጥ የሚታየው፣ [እንደ አባትዋ] ለሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ አፅንዖት ለመስጠት ሲፈለግ ነው። አፅንዖት መስጠት ግን አንድን ሀረግ ወይም አረፍተ ነገር በጥቅም ላይ ስናውል፣ ከስሜት ጋር ተጣምሮ የሚመጣ የአጠቃቀም ባህሪ እንጅ፣ መሰረታዊ የሀረግ አወቃቀር ስርዓት አይደለም። ምክንያቱም የአንድ ሀረግ መሰረታዊ የመዋቅር ቦታ የሚወሰነው በሀረጉ ሰዋስዋዊ ተግባር እንጅ፣ በሀረጉ አጠቃቀም ላይ፣ ማለትም ሀረጉ በንግግር ላይ ሲውል በተጠቃሚዎች ላይ በሚፈጥረው ስሜት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ነው። መሰረታዊ መዋቅራዊ (ሰዋስዋዊ) ተግባር የምንላቸው፣ መሪነት፣ መሙሊያነት፣ አጎላማሽነትና መስተዓምርነት ናቸው። ያም ሆኖ፣ 7(ሀ) እና (ለ) በተራ ቁጥር (6) የተመለከተው ቅፅላዊ ሀረግ ሳፅሳይ ቅርፅ ናቸው።

## ግሳዊ ቅፅል

ግሳዊ ቅፅል የሚባሉት ከግስ ስር ላይ የሚመሰረቱ ቅፅሎች ናቸው። እንደሚመሰረቱበት ስር፣ መዋቅራዊ ባህሪ መሙሊያ የሚፈልጉና የማይፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ለሰው ያዘናል 1
(ለ) የሰው አዛኝ

1(ሀ) ግሳዊ ሀረግ ሲሆን፣ መሪው ያዝናል የሚለው ግስ ነው። በባህሪው መሙሊያ የሚፈልግ ግስ አይደለም። ገላጭ ሀረግ ግን እንደ ማንኛውም ግስ ይፈልጋል። ለሰው የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ለዚሁ ተግባር የገባ ነው። አዛኝ የሚለው ውልድ ቅፅል ሲሆን፣ መሰረቱ ያዝናል የሚለው ግስ የተወለደበት ስር ነው። እሱም እንደ ግሱ መሙሊያ አይፈልግም። ገላጭ ሀረግ ግን ሊፈልግ ይችላል። የሰው የሚለው ሀረግ የገባው ለዚሁ የገላጭነት ተግባር ነው። ቅፅሉና ግሱ ከአንድ ስር ስለተመሰረቱ መዋቅራዊ ባህሪ ሊጋሩ ችለዋል። በግሳዊ ሀረጉ ውስጥ ለሰው የሚለው ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረግ፣ በቅፅላዊ ሀረጉ ውስጥ የሰው በሚል ስማዊ ሀረግ መልክ ገብቶአል።

ነባር ቅፅሎች መሙሊያ የላቸውም። ውልድ የሚባሉትም ቢሆኑ፣ ከጥቂቶቹ በስተቀር፣ መሙሊያ የላቸውም። ለዚህም ምክንያቱ የሚመሰረቱበት ስር በመዋቅራዊ ባህሪው መሙሊያ የሚፈልግ ባለመሆኑ ነው። ከውልድ ቅፅሎች መካከል መሙሊያ አላቸው ሊባሉ የሚችሉት እንደ አታላይ ያሉት ብቻ ናቸው። ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል።

[ሽማግሌ አታላይ] 2

አታላይ የሚለው ቅፅል አታለለ የሚለው ግስ ከተመሰረተበት ሳቢ ስር የወጣ ነው። ግሱ መሙሊያ እንደሚፈልግ ሁሉ፣ ቅፅሉም እንደዚሁ ይፈልጋል። ይህን ፍላጎቱን ለማሙዋላት ሽማግሌ ከሚለው ስም ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ መስርቶአል። ከዚህ በመነሳት፣ ግሱም ሆነ ቅፅሉ እኩል ሳቢ ናቸው ለማለት ይቻላል። ከዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባ አንድ ጉዳይ አለ፡፡ ይህም ስሮች ሳቢና ኢሳቢ ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉና ከእነሱ የሚወለዱ ሁሉ፣ ይህን የሳቢነት ወይም የኢሳቢነት ባህሪ የሚወርሱ መሆናቸው ነው፡፡

ግሳዊ ቅፅል አቢይ ሀረግ ለመመስረት ከተለያዩ አጎላማሽ ሀረጎች ጋር እንደሚከተለው ሊዋቀር ይችላል።

[እንደ ካሳ [ሽማግሌ አታላይ]] የለም 3

[እንደ ካሳ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። እገባቡ [ሽማግሌ አታላይ] የሚለውን ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ ቀድሞ ነው። ተግባሩም ይህንኑ ንዑስ ሀረግ እያነፃፀሩ ማጎላመስ ነው። ንፅፅሩ ከሌላ በግሀድ ከማይታይ ሀረግ ጋር ነው። በግሀድ ሲታይ ሀረጉ የሚከተለውን ይመስላል።

እሰቴር [እንደ ካሳ [ሽማግሌ አታላይ]] ነች 4


ከእረፍት ነገሩ ትርጉም ስመረዳት እንደሚቻለው፣ ካሳ እና እሰቴር እኩል [ሽማግሌ እታላይ] ናቸው። እንደ የሚለው መሰተዋድድም አነፃፃሪ ነው።

[እንደ ካሳ ሽማግሌ እታላይ] የሚለው አንድ አሀዳዊ ሀረግ መሆኑን ከሚከተለው ምሳሌ ማረጋገጥ ይቻላል።

(ሀ) [እንደ ካሳ ሽማግሌ እታላይ] [እሰቴር [ — ] ነች] 5
(ለ) እስቴር [እንደ ካሳ [ሽማግሌ እታላይ]] ነች፣ አልማዝስ?
(ሐ) እሱዋ እንኩዋ [ — ] አይደለችም

በምሳሌ (4) [እንደ ካሳ ሽማግሌ እታላይ] የሚለው ሀረግ ነች ከሚለው ግስ በፊት ገብቶአል። ይሀ መሰረታዊ ቦታው ነው። በምሳሌ 5(ሀ) ውስጥ፣ ይኸው ሀረግ እስቴር የሚለውን የእረፍተ ነገሩን ባለቤት ቀድሞ ገብቶአል። ይህን ያደረገው በተራ ቁጥር (4) የነበረበትን መሰረታዊ ቦታውን በመልቀቅ ነው። የለቀቀውም ያለ ምንም ቀሪ እንደ አንድ አካል ሆኖ ከቦታው በመንቀሳቀስ ነው። ይህም ቅንጅቱ አንድ መዋቅር ስመሆኑ ማስረጃ ነው። በተጨማሪም፣ በምሳሌ (ሐ) ውስጥ ይኸው ሀረግ ከቦታው ተገድፎአል። የተገደፈውም እሁንም ያለ ምንም ቀሪ ነው። ቅንጅቱ አንድ አሀዳዊ መዋቅር ባይሆን ኖሮ፣ የዚህ ምሳሌ ተቀባይነት አጠራጣሪ ይሆን ነበር።

የሀረጉን ውስጣዊ አቀነጃጀት እንደሚከተለው በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን።



6

እንደ በሚለው መስተዋድድ አማካኝነት የሚመሰረቱ እንደ ካሳ ያሉ ንፅፅራዊ የመስተዋድድ ሀረጎች እስቴርና ካሳ እኩል እታላይ መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው። ይህን እቻነት የሚያሳየው እንደ የሚለው መስተዋድዳዊ መሪ ነው። ከዚሀም የተነሳ ይህን መሪ አደላዳይ መስተዋድድ ልንለው እንችላለን። አደላዳይ ማለትም እኩል አድራጊ ማለት ነው። የሚከተለውን ደግሞ እንመልከት።

አስቴር [እንደ ካሳ [ጨለማ ደፋር] ] ነች 7


ደፋር የሚለው ደፈረ የሚለው ሳቢ ግስ ከተመሰረተበት ስር ላይ የተመሰረተ ቅፅል ነው። ስለዚህም እሱም እንደ ግሱ ሳቢ ነው። በመሆኑም መሙሊያ ይፈልጋል። ስለዚህም ጨለማ ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ [ጨለማ ደፋር] የሚለውን ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ መስርቶአል። ይህ ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ ደግሞ [እንደ ካሳ] ከሚለው አነፃፃሪ የንፅፅር መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ [እንደ ካሳ [ጨለማ ደፋር]] የሚለውን አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ መስርቶአል።

ይህ አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ በጣም ከሚለው መጣኝ መስተዓምር ጋር ተዋቅሮ ዋናውን አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ እደሚከተለው ይመሰርታል።

[በጣም [እንደ ካሳ [ጨለማ ደፋር] ] ] 8

ይህ አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ፣ በዕፀ-መዋቅር ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል።

9




ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ ዋናው ቅፅላዊ ሀረግ (ቅሀ) ከመጣኝ መስተዓምርና ከአቢዩ ቅፅላዊ ሀረግ (ቅሀ2) የተዋቀረ ነው። ቅፅላዊው ሀረግ የዋናው ሀረግ መሪ ነው። ይህ መሪ ሀረግ (ቅሀ2) ከአነፃፃሪ መስተዋድዳዊ ሀረግና ከንዑሱ ቅፅላዊ ሀረግ (ቅሀ1) ጋር ተዋቅሮአል። ንዑሱ ቅፅላዊ ሀረግ የአቢዩ ሀረግ መሪ ነው። በመጨረሻም

ንዑሱ ቅፅላዊ ሀረግ ጨለማ ከሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግና ደፋር ከሚለው ቅፅል ጋር እንደተዋቀረ እናያለን። ቅፅሉ የንዑሱ ሀረግ መሪ ነው።

እስካሁን ያየነው የአወቃቀር ስርዓት ከግሳዊ ሀረግና ከስማዊ ሀረግ ስርዓት ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው። በሁሉም ውስጥ መስተዓምር፣ አጎላማሽና መሙሊያ አለ። የእያንዳንዳቸው ወርዳዊና ተዋረዳዊ አገባብም አንድ አይነት ነው። በሁሉም ሀረጎች መስተዓምሩ ያቀድማል፤ ገላጩ ይከተላል፤ መሙሊያው ይቀጥልና መሪው መጨረሻ ላይ ይመጣል። በሶስቱ የሀረግ አይነቶች መካከል ያለው ልዩነት በመሙሊያው ላይ ነው። ይኸውም የስማዊና የቅፅላዊ ሀረግ መሙሊያ በቦታው ሊገኝ ወይም ላይገኝ ይችላል። የግሳዊ ሀረግ መሙሊያ ግን የግድ በቦታው መገኘት አለበት። መስተዓምሮችና አጎላማሾች በሶስቱም የሀረግ አይነቶች ውስጥ በቦታቸው ላይገኙ ይችላሉ። ከዚህ ስንነሳ በሶስቱም ሀረጎች ውስጥ ከቦታው መጥፋት የሌለበት የግስ መሙሊያ ብቻ ነው። ይህም ግስን ከስምና ከቅፅል የምንለይበት ዋና መዋቅራዊ ባህሪ ነው። ቅፅልንም ከስም የምንለይበት መዋቅራዊ ባህሪ አለ። እሱም የአጎላማሹ አይነትና ተግባር ነው። እስተውስን ከሆነ፣ የቅፅል አጎላማሽ ሁል ጊዜ ንፅፅራዊ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው።

## ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ

ባለፉት ንዑስ ክፍሎች የስማዊ፣ የግሳዊና የቅፅላዊ ሀረጎችን የአወቃቀር ስርዓት ለማየት ሞክረናል። ሁሉም ንዑስ ሀረጋቸውን ከመሙሊያ ሀረጎችና ከመሪዎች፣ አቢይ ሀረጋቸውን ከተለያዩ አጎላማሽ ሀረጎችና ከንዑስ ሀረግ እንደሚመሰርቱ ተረድተናል። አቢይ ሀረጎቹ ደግሞ በተራቸው ከመስተዓምሮች ጋር እየተዋቀሩ ዋናውን አቢይ ሀረግ ሲመሰርቱ አይተናል። በሁሉም ሀረጎች ውስጥ የመሪው ቦታ በስተቀኝ ነው። ይህ ያወቃቀር ስርዓት ተውሳከ ግሳዊ ሀረጎችንም ሊያጠቃልል ይችል እንደሆነ፣ ከዚህ ቀጥለን እንመረምራለን።

ዶጋግመን እንደጠቀስነው፣ ተውሳከ ግስ የሚባለው ክፍል እንደሌሎቹ ክፍሎች በርካታ ቃላት የሉትም። ባንፃሩ ግን የተለያዩ ተውሳከ ግሳዊ የሚባሉ በርካታ ተግባራት አሉ። እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

የሁኔታ 1
የጊዜ
የምክንያት
የማድረጊያ
የቦታ
የንፅፅር
ወዘተ

እነዚህ ተውሳከ ግሳዊ ተግባራት የሚገለፁት በአብዛኛው በስማዊ ሀረግ፣ በመስተዋድዳዊ ሀረግና በጥገኛ አረፍተ ነገሮች አማካኝነት ነው። በዚህም ምክንያት፣ እንደነዚህ ያሉ ሀረጎችን ብዙ ጊዜ ተውሳከ ግሳዊ ሀረጎች እንላቸዋለን።

በቋንቋዋው ውስጥ የሚገኙት ጥቂት መደበኛ ተውሳከ ግሶች የሚከተሉት ናቸው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| (ሀ) | ቶሎ | (ለ) | ክፉኛ | 2 |
| | ገና | | ግምኛ | |
| | እንደገና | | ድልና | |
| | መቼ | | ምንኛ | |

በ(ሀ) ስር ያሉት ነባር ተውሳከ ግሶች ሲሆኑ፣ በ(ለ) ስር ያሉት ግን /-ኛኛአ/ በሚለው መስራች ምዕላድ አማካኝነት ከቅፅሎች ላይ እንደሚመሰረቱ በምስረታው ክፍል ተመልከተናል።


ተውሳከ ግሶች መሙሊያ የላቸውም። ስለዚህም ንዑስ ሀረጋቸውን የሚመሰርቱት በመሪው ቃል ብቻ ነው። በዚህ መዋቅራዊ ባህሪያቸው ከሌሎቹ የቃላት ክፍሎች ይለያሉ። ቀደም ሲል በተከታታይ እንዳየነው፣ ሌሎቹ ክፍሎች በከፊልም ቢሆን፣ መሙሲያ አላቸው። በግስ ክፍል ውስጥ፣ ሳቢ ግሶች ያለመሙሊያ አይቆሙም። ስሞችና ቅፅሎችም ከመሙሊያ ጋር ሲዋቀሩ ይችላሉ። ርግጥ፣ መሙሊያዎቹ ቀሪ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ረገድ ተውሳከ ግሶች ልዩ ናቸው። ከሌሎቹ ጋር የሚመሳሰሉት በአቢይ ሀረግ ደረጃ ብቻ ነው። ምክንያቱም በዚህ ደረጃ እንደ ማንኛውም የሀረግ ክፍል ከመስተዋድዳዊ ሀረግና ከመጣኝ መስተዓምር ጋር ሲዋቀሩ ይችላሉ። መስተዋድዳዊ ሀረጉ ግን የተወሰነ ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) አስቴር [እንደ ካሳ [ክፉኛ]] ወደቀች 3

(ለ) እለቴር [እንደ ካሳ [ቶሎ]] ተነሳች

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ [እንደ ካሳ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፣ ቅንጅቱም በውስጠኛው ቅንፍ ውስጥ ከሚታዩት [ክፉኛ] እና [ቶሎ] ከሚሉት ተውሳከ ግሶች ጋር ነው። ተግባሩም የአስቴርን የአወዳደቅ ሁኔታ ከካሳ የአወዳደቅ ሁኔታ ጋር ማነፃፀር ነው። ስለዚህም ንፅፅራዊ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። መዋቅራዊ ስርዓቱን በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።

4





[እንደ ካሳ] የሚለው ንፅፅራዊ ሀረግ ተግባር፣ የአወዳደቁን ወይም የአመጣጡን ሁኔታ፣ ማለትም መጥፎነቱን ወይም ፍጥነቱን፣ መግለፅ ነው። መጥፎነቱም ሆነ ፍጥነቱ የሚገለፀው ደግሞ [ከፉኛ] እና [ቆሉ] በሚሉት ተውሳከ ግሶች ስለሆነ፣ የመስተዋድዳዊ ሀረጉ መዋቅራዊ ግንኙነትም ከነዚሁ ተውሳከ ግሶች ጋር ነው። ተውሳከ ግሶቹ በሀረጉ በስተቀኝ ስለሚገኙ፣ ሀረጉ ቀኝ መሪ ነው።

ከዚህ ላይ የተውሳከ ግስንና የቅፅልን መዋቅራዊ ባህሪ ተመሳሳይነት ልብ ልንል ይገባል። የሁለቱም ገላጭ ሀረግ ንፅፅራዊ መስተዋድድ ነው። ሁለቱም ከፍሉች ገላጭ ስለሆኑ፣ የተግባር አንድነት አላቸው። ይህ የተግባር አንድነት መዋቅራዊ ተመሳሳይነትን ሊያስከትል ችሉአል። በመካከላቸው ያለው ልዩነት በንዑስ ሀረግ ደረጃ ነው። ቅፅሎች መመሲያ ሲኖራቸው፣ ተውሳከ ግሶች የላቸውም።


ቀደም ሲል ስለ ቅፅላዊ ሀረግ ስንወያይ እንዳየነው፣ [እንደ ካሳ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ግንኙነት ከተውሳከ ግሱ ጋር ሳይሆን፣ ከእሱ ጋር ከተዋቀረው ግሳዊ ሀረግ ጋር ነው፤ ሊባል ይችላል። ይህም ማለት፣ ለምሳሌ፣ በመጀመሪያው አረፍተ ነገር ውስጥ፣ [እንደ ካሳ] የሚለው ሀረግ ግንኙነት [ከፉኛ] ከሚለው ተውሳከ ግስ ጋር ሳይሆን፣ [ከፉኛ ወደቀ] ከሚለው ግሳዊ ሀረግ ጋር ሊሆን ይችላል። ይህም ሲሆን፣ ንፅፅራዊ ገላጭነቱ በተውሳከ ግሱ ለተገለፀው <u>ሁኔታ</u> ሳይሆን፣ በግሱ ለተገለፀው <u>ድርጊት</u> ሊሆን ይችላል። የመስተዋድዳዊው ሀረግ አገባብ አሻሚ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ንፅፅራዊ ሀረጉ ግሳዊንም ሆነ ተውሳከ ግሳዊ ሀረግን ሊገልፅ የሚችል መሆኑ ነው። ከተውሳከ ግሱ ጋር ያለው አቀነጃጀት ከፍ ሲል እንደተመለከተው ሲሆን፣ ከግሳዊ ሀረጉ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ደግሞ ከዚህ በታች እንደሚታየው ነው።

5




መስተዋድዳዊ ሀረጉ የተውሳከ ግሱ ወይም የግሳዊ ሀረጉ አጎላማሽ ሊሆን እንደሚችል ዕፀ-መዋቅሮቹ ያመለክታሉ። እንደዚህ አይነቱ መዋቅራዊ አሻሚነት፣ በመዋቅር ደረጃ፣ በዚህ አይነት ሊፈታ ይችላል። ከመዋቅር ባሻገር ግን፣ ለምሳሌ፣ በንግግር ጊዜ፣ አሻሚነቱ ሊፈታ የሚችለው፣ በንግግሩ አውድ ብቻ ነው።

ከፍ፡ ሲል እንደገለፅነው፣ ተውሳከ ግሳዊ ሀረጎች [በጣም] ከሚለው መጣኝ መስተዓምር ጋር ሊዋቀሩ ይችላሉ። የመስተዓምሩ ቦታም እንደ ማንኛውም መስተ-ዓምር በሀረጉ መነሻ ላይ ሲሆን፣ ተግባሩም በሀረጉ የተገለፀውን ሁኔታ ከመጠን አንፃር መወሰን ነው። ለምሳሌ፣ [ክፉኛ] ወይም [ቶሎ] ስንል፣ የፍጥነቱን ወይም የክፋቱን ደረጃ አናውቅም። ይህ የሚታወቀው [በጣም] የሚለውን መስተዓምር በመጠቀም [በጣም ቶሎ] ወይም [በጣም ክፉኛ] ስንል ነው። አቢይ ሀረጉ ውስጥ [በጣም] የሚገኘው በሀረጉ መነሻ ላይ ነው። ከዚህ አንፃር የሚከተለውን እንመልከት፡




6

ዕፀ-መዋቅሩ [በጣም] የሚለው መስተዓምር ከአቢዩ ሀረግ *እንጉዎ* ላይ እንደሚወርድና በሀረጉ መነሻ ላይ እንደሚገኝ ያሳያል። ይህ ግን በታህታይ መዋቅር ውስጥ የሚታይ ቅደም-ተከተል ነው። በላዕላይ መዋቅሩ ውስጥ፣ መስተዋድዳዊ ሀረጉ ከቦታው እየተነሳ ወደ አቢይ ሀረጉ መነሻ ስለሚሄድ፣ መስተዓምሩ ከመሪው፣ ማለትም ከ[ቶሎ] ቀድሞ የገባ ሊመስል ይችላል። ይህ ሲሆን ሀረጉ እንደሚከተለው ይሆናል።

[እንደ ካሳ [በጣም [—] ቶሎ ]] 7

በግልፅ እንደሚታየው፥ [እንደ ካሳ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ በነጠብጣብ የተመለከተውን መሰረታዊ ቦታውን ለቆ፣ በሀረጉ መነሻ ላይ ገብቶአል። ይህ ሁኔታ በቅፅላዊ ሀረግም ይታያል። የሚከተለውን እንመልከት።

[እንደ ካሳ [በጣም [—] ረዥም]] 8

ይህ አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ ነው። መሪው [ረዥም] የሚለው ቅፅል ነው። የሀረጉ ታህታይ አወቃቀር እንደሚከተለው ነው።

[በጣም[ እንደ ካሳ [ረዥም]]] 9

ይህ መዋቅር ከላይ በተራ ቁጥር (7) ከሚታየው ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው። በሁለቱ ሀረጎች መካከል ያለው ልዩነት የአወቃቀር ሳይሆን፣ የአይነት ብቻ ነው። ይኸውም አንዱ ተውሳከ ግሳዊ ሲሆን፣ ሌላው ቅፅላዊ መሆኑ ነው። የሁለቱ መዋቅር ይህን ያህል ተመሳሳይ የሆነው ያለምክንያት አይደለም። ከፍ ሲል እንደገለፅነው፣ ሁለቱም ገላጮች ናቸው። ተውሳከ ግሶቹ ግሰን፣ ቅፅሎቹ ስምን ይገልፃሉ። ስምና ግስ ተገላጭ፣ ቅፅልና ተውሳክ ግስ ገላጭ እንደሆኑ፣ በምዕራፍ ሁለት ስለ ቃላት ክፍል ስንወያይ ገልፀናል፡፡

ወደ መስተዓምሩ እንመለስና አንድ ጥያቄ እናንሳ። ይኸውም [በጣም] የሚለው መጣኝ መስተዓምር ታህታይ ቦታ በሀረጉ መነሻ ላይ ስመሆኑ ማሰረጃው ምንድን ነው? የሚል ነው። ቀደም ሲል ሌሎቹን አስመልክተን እንደ ገለፅነው ሁሉ፣ አንድ መሪ ቃል ንዑስ ሀረጉን የሚመሰርተው ከመሙሊያ ጋር በመዋቀር ወይም ያለ መሙሊያ ብቻውን በመቆም ነው። ምርጫው መሙሊያ በመፈለግና ባለመፈለግ ነው። በማንኛውም መንገድ የተዋቀረ ንዑስ ሀረግ የተለያዩ ገላጮች ያስፈልጉታል። ገላጮቹ ሀረጉን ከጊዜ፣ ከምክንያት፣ ከዓላማ፣ ከማድረጊያ፣ ወዘተ፣ አኩዋያ ተጨማሪ መረጃ በመስጠት በቅርፅም ሆነ በይዘት ያጎላምሉታል። በዚህ ሁኔታ ያደገ ሀረግ መጠኑን የሚገለፅበት መጣኝ ሀረግ ያስፈልገዋል።

መጣኞቹ እንደ [በጣም] ያሉ የመጠን መስተዓምሮች ናቸው። ቦታቸውም ከፍ ሲል እንደገለፅነው፣ በሀረጉ መነሻ ላይ ነው። ይህ የሚሆንበት ምክንያት በሀረጉ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቦታዎች በሙሉ ሀረጉን እየሞሉና እያጎላመሉ በሚገቡት መሙሊያዎችና ገላጮች ስለሚያዙ ነው። አንድ መሪ ሀረጉን መዞና አሳድጎ የሚጨርሰው በመሙሊያዎችና በገላጭ አጎላማሾች ነው። በእነዚህ እየታጀበ ካደገ በሁዋላ መጠኑን የሚያሳይበት መጣኞች፣ የትነቱን የሚያሳይበት ጠቋሚዎች፣ እንዲሁም የማንነቱን የሚያሳውቅበት አገናዛቢዎች ያስፈልጉታል። እነዚህም ሊገቡ የሚችሉት በመነሻው ላይ ነው። የሀረጉን ይዘት ሊወስኑ የሚችሉት ሙሉ ሀረጉን እየቀደሙ በመነሻ ላይ ሊገቡ ነውና። ከሀረጉ መሀል ቢገኙ፣ ሊወስኑ የሚችሉት ሙሉውን ሀረግ ሳይሆን፣ ከሚገኙበት ቦታ ጀምሮ ያለውን የሀረጉን ከፊል አካል ብቻ ይሆናል። በሌሎቹ ሀረጎች ያየነው ሁኔታም እንደዚሁ ነበር። መስተዓምሮቹ የየሀረጉ መነሻ ናቸው። በዚህም የተውሳክ ግስን ብቻ ሳይሆን የዋና ዋናዎቹን የቃላት ክፍሎች የሀረግ አወቃቀር ስርዓት እናጠቃልላለን።

## መስተዋድዳዊ ሀረግ

እስካሁን ያየነው የዋና ዋና ቃላት ክፍሎችን የሀረግ አወቃቀር ስርዓት ነው። ዋና ዋና የቃላት ክፍሎች የሚባሉት፣ ትርጉም ወይም ይዘት ያላቸው ክፍሎች ናቸው። እነዚህም የስም፣ የግስ፣ የቅፅልና የተውሳከ ግስ ክፍል ቃላት ናቸው። ሌሎቹ የቃላት ክፍሎች መስተዋድድና መስተዓምር ናቸው። እነዚህ የይዘት ሳይሆን፣ የግብር ቃላት ክፍሎች ናቸው። ከዚህ ቀጥለን የነዚህን ሁለት ክፍሎች ስርዓት-መዋቅር እንመለከታለን። መጀመሪያ የመስተዋድዶችን እንመልከት።

እንደ ሌሎች የቃላት ክፍሎች ሁሉ፣ መስተዋድዶችም ንዑስና አቢይ ሀረጎችን ይመሰርታሉ። ንዑስ ሀረጎችን የሚመሰርቱት ከመሙሊያዎች ጋር በመዋቀር ነው። መሙሊያዎቹም ስማዊ ሀረጎች፣ መስተዋድዳዊ ሀረጎችና አረፍተ ነገሮች ናቸው።

እንደ መሙሊያቸው አያነት መስተዋድዶችን በሁለት ክፍለን ልናያቸው እንችላለን። ይኸውም ከስማዊ ሀረግና ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር የሚዋቀሩትን በአንድ በኩል፣ ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩትን በሌላ በኩል በመመደብ ነው። ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩት በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ጥገኛ መስተፃምር ይባሉ የነበሩት ናቸው። እኛ ምይ ብለናቸዋል። ምክንያቱም ተግባራቸው ማጣመር ሳይሆን፣ እንደ አረፍተ ነገር በመሙሊያነት ወይም በአጎላማሽነት በሌላ አረፍተ ነገር ውስጥ ጥገኛ ሆኖ መግባቱን ማመልከት ስለሆነ ነው።

በዚህ ንዑስ ክፍል የምናተኩረው ከስማዊ ሀረግና ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር በሚዋቀሩት መስተዋድዶች ላይ ነው። በክፍል ሁለት እንደገለፅነው፣ መስተዋድድ የሚባለው ክፍል እንደ ሌሎቹ ክፍለ-ቃላት እንደ ስሞች፣ ግሶችና ቅፅሎች የነገሮች፣ የድርጊቶችና የባህሪያት ስያሜ አይደለም። የግብር ቃላት ናቸው። ግብራቸውም በቀደምት ሊቃውንት በሚገባ እንደሚታወቀው፣ ማያያዝ ወይም ማዋደድ ነው። ይህን ተግባር ለመፈፀም የሚያስፈልገው የአያያዥ መጠን በሚያያዙት ነገሮችና በሚፈፅሙት ሰዋስዋዊ ተግባር ልክ ይወሰናል። የሚያያዙት ነገሮች ደግሞ ስሞች፣ ግሶች፣ ቅፅሎችና ተውሳከ ግሶች ናቸው። ተግባራቱም በተውሳከ ግሱ ክፍል የተዘረዘሩት ናቸው። እነዚህን ለመግለፅ የቃላቱ ክፍል ርስበርስ ሲዋቀሩ አንዱን ተዋቃሪ ከሌላው ጋር ለማያያዝ የሚያስፈልገው የአያያዥ ቃላት መጠን ጥቂት ነው። በዚህ ምክንያት በቋንቋዋው ውስጥ የሚገኙት መስተዋድዶች የሚከተሉት ናቸው።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ስለ | እንደ | ጋር | እስከ | ወደ | 1 |
| ላይ | ለ- | ስ- | በ- | ከ- | |

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ መስተዋድዶች በራሳቸው ምንም ትርጉም የላቸውም። ራሳቸውንም ችለው መቆም አይችሉም፣ ሁል ጊዜ ድጋፍ ይፈልጋሉ። ባጭሩ ተለጣፊ ናቸው። የሚለጠፉት መሙሊያ ሆኖ በሚገባው ሀረግ መነሻ ላይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙና እንፃራዊ ትርጉም ያላቸው ጥቂት መስተዋድዶች አሉ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አጠገብ | ባሻገር | በኩል | | |
| በስቲያ | ድረስ | ማዶ | አኩዋያ | 2 |

እነዚህ መስተዋድዶች አንድን ነገር፣ አንድ ሌላ ነገር ከሚገኝበት ቦታ አንፃር የሚገልፁ ናቸው። ለምሳሌ፣ ወንበሩ ከጠረጴዛው አጠገብ ነው ፣ ስንል፣ ጠረጴዛው የሚገኝበትን ቦታ እንደመነሻ ወስደን፣ ወንበሩ ከዚያ መነሻ ቦታ አንፃር፣ ምን ያህል እንደሚርቅ ወይም እንደሚቀርብ መግለፃችን ነው። አጠገብ የሚለው በሁለቱ ነገሮች መካከል ያለውን ቅርበት ያመለክታል። እንደ አጠገብ ያሉ ራስ ቻይ መስተዋድዶች መሙሊያቸውን ተከትለው ሲገቡ፣ ተለጣፊዎቹ ቀድመው ይገባሉ። ይህ ግን በላዕላይ መዋቅር ደረጃ ነው።


አሁን ወደ ዝርዝር መዋቅራዊ ባህሪያቸው እንሂድ። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ መስተዋድዶች ከስማዊ ሀረግና ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር እየተዋቀሩ ንዑስ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሊመሰርቱ ይችላሉ። የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው።

(ሀ) [ወደ [ትልቁ ትምህርት ቤት]] 3

(ለ) [[እስከ [ትልቁ ትምህርት ቤት]] ድረሰ]

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ <u>ወደ</u> የሚለው መስተዋድድ [ትልቁ ትምህርት ቤት] ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮአል። ስማዊ ሀረጉ መሙሊያ ነው። መሪው መስተዋድድ ከዚሁ ሀረግ ቀድሞ ገብቶአል። አገባቡም ትልቅ የሚለው ተለጣፊ በመሆን ነው። ተለጣፊነቱ በተለይ <u>ወደቤት</u> ለንልና ለንፅፍ የጎላ ነው።


በምሳሌ (ለ) ውስጥ፣ <u>ድረሰ</u> የሚለው መስተዋድድ [እስከ ትልቁ ትምህርት ቤት] ከሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮአል። አገባቡ መሙሊያውን ተከትሎ ነው። የሁለተኛውን ሀረግ ያወቃቀር ስርዓት በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተሰው እናሳያለን።




4

በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>ድረሰ</u> የሚለው መሪ መስተዋድድ ነው። [እስከ ትልቁ ትምህርት ቤት] የሚለውን መድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግ ተከትሎ በስተቀኝ በኩል ገብቶአል። <u>እስከ</u> የሚለው የመሙሊያው መስተዋድዳዊ ሀረግ መሪ ነው። እሱም [ትልቁ ትምህርት ቤት] የሚለውን መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ቀድሞ ገብቶአል። ሁኔታው የሁለቱ የመነሻና የመድረሻ መስተዋድዶች አገባብ ለየቅል መሆኑን ያስረዳል። ይህም ልዩነት ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ምናልባት ከመሪዎቹ መስተዋድዶች ራስን ችሎ ከመቆምና ካለመቆም የሚመጣ ሊሆን ይችላል። ራሳቸውን ችለው የሚቆሙት መሪዎች መሙሊያውን ተከትለው ሲገቡ፣ ራሳቸውን ችለው የማይቆሙት፣ መሙሊያውን እየቀደሙ ይገባሉ። አገባባቸውም በተለጣፊነት ነው። ይህ ልዩነት ግን መሰረታዊ ሳይሆን፣ በመዋቅሩ ላዕላይ ገፅታ ላይ የሚከሰት የመሪና የመሙሊያ ዝምድና ነው፣ ለማለት ይቻላል። በመሰረታዊ (ታህታይ) አወቃቀር ደረጃ ላይ፣ የማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ መሪ ቦታ ከመሙሊያው

በስተቀኝ በኩል ነው፣ ብሎ ማሰብ ይቻላል። በዚህም መሰረት፣ በተራ ቁጥር (4) የሚታየው መዋቅር ታሀታይ አወቃቀር እንደሚከተለው ይሆናል።




5

ይህ መዋቅር መስተዋድዳዊ መሪዎቹ ከመሙሊያዎቹ በስተቀኝ እንደገቡ ያሳያል። ይህም የማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ ስርዓት ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ መሪው ከመሙሊያው እየቀደመ የሚገባው በላዕላይ መዋቅር ነው። በተራ ቁጥር (4) የሚታየውም ይኸው ነው።

የመሪው ቦታ ከመሙሊያው በስተቀኝ ለመሆኑ ማስረጃው ሌሎቹ ቀደም ሲል ያየናቸው ሀረጎች መሪ በስተቀኝ መሆኑ ነው። ለምሳሌ ትልቁ ትምህርት ቤት የሚለው ስማዊ ሀረግ መሪ ትምህርት ቤት የሚለው ጥምር ስም ሲሆን፣ ቦታውም በስተቀኝ ነው። እንደ ካሳ ሽማግሌ ደፋር የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ መሪም ደፋር የሚለው ቅፅል ሲሆን፣ የእሱም አገባብ እንደዚሁ በቀኝ በኩል ነው። ባለፈው ንዑስ ክፍል ያየነው የግሳዊ ሀረግ ስርዓትም እንደዚሁ ነው። ከዚህ አጠቃላይ የአገባብ ሁኔታ ስንነሳ፣ ሀረጎች በሙሉ ቀኝ መሪ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል።

ከላይ የሚታዩት የንዑስ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ምሳሌ ናቸው። ከዚህ ቀጥለን የአቢይ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን መዋቅር እንመለከታለን።

(ሀ) [ከወገብ [በታች]] 6
(ለ) [እንደ አሳ [በባህር]]

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ በታች የሚለው ክፍል ንዑስ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። መሪው በ የሚለው መስተዋድድ ሲሆን፣ መሙሊያው ታች የሚለው ስም ነው[12]። በምሳሌ (ለ) ውስጥ፣ ደግሞ ይኸው መስተዋድድ ባህር ከሚለው ስም ጋር ተዋቅሮአል። እነዚህ ንዑስ ሀረጎች ከወገብ እና እንደ አሳ ከሚሉት ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር ተዋቅረው አቢይ መስተዋድዳዊ ሀረግ መስርተዋል። ከወገብ የሚለው ገላጭ

12 ስም ነው ከማለት ይልቅ መስተጻምር ነው ማለቱ ይቀላል፡፡ ሁኔታውን ወደሁዋላ እናየዋለን፡፡